
ኅብረት ለምርጫ(CECOE)

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Elections




# የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ-ውሳኔ እና የወላይታ ዞን ድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ አጠቃላይ የትዝብት ሪፖርት

www.cecoe.org

ነሐሴ
2015

## ስለ ኅብረት ለምርጫ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) ከ 175 በላይ አገር በቀል የሲቪል ማህበራት ስብስብ ሲሆን፤ ለትርፍ ያልተቋቋመ እና መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 1113/2011 መሰረት፣ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 4748 ጥር 25 ቀን 2012 ሕጋዊ ሰውነቱን ያገኘ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው፡፡

ኅብረት ለምርጫ የተመሰረተው የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት፤ በምርጫ ትዝብት እና ክትትል፣ በመራጮች ትምህርት እና ከምርጫ በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን በመከላከል ላይ ያላቸውን ሚና ለማሳደግ እና ለማስተባበር ነው፡፡

## ማሳሰቢያ

ይህ ሪፖርት ሊሳካ የቻለው እና የታተመው በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ(USAID)፣ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም(NDI)፣ በዴንማርክ ኤምባሲ፣ በአየርላንድ ኤምባሲ እና በአውሮፓ የምርጫ ድጋፍ ማዕከል(ECES) ባደረጉት ልባዊ ድጋፍ ነው፡፡ ይዘቱ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ ኃላፊነት እንጂ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ፣ የዴንማርክ ኤምባሲ፣ የአየርላንድ ኤምባሲ ወይም ሌሎች አጋር ድርጅቶችን አቋም እና ምልከታ የሚያንፀባርቅ አይደለም፡፡

# ማውጫ

**የቃላት መፍቻ**........................................1

**ዋና ማጠቃለያ**........................................3

የግኝቶች ማጠቃለያ........................................3

ዋና ዋና ምክረ-ሃሳቦች........................................ 5

**መግቢያ**........................................ 6

**ክፍል አንድ**

**ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄደው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት**...........7

ምዕራፍ 1: ሕዝበ -ውሳኔው የተካሄደበት የፖለቲካ አውድ ........................8

ምዕራፍ 2: የሕዝበ-ውሳኔ ምርጫ እና የምርጫ ትዝብት የሕግ ማዕቀፍ .............9

ምዕራፍ 3 ፥ የትዝብት ዘዴ ........................................12

ምዕራፍ 4 ፥ የትዝብት ግኝቶች ........................................15

ምዕራፍ 5: ማጠቃለያ እና ምክረ-ሃሳቦች ........................................27

**ክፍል ሁለት**

**የወላይታ ዞን ድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ ትዝብት** .......................29

ምዕራፍ 6: መግቢያ ........................................30

ምዕራፍ 7: የቅድመ -ድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት ግኝቶች........................31

ምዕራፍ 8: የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ቀን የትዝብት ግኝቶች........................33

ምዕራፍ 9: የድህረ -ድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ የትዝብት ግኝቶች........................38

ምዕራፍ 10: መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳቦች ........................................38

# የቃላት መፍቻ

| | |
|---|---|
| ኅብረት ለምርጫ (ኅብረቱ). . . . . | የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ |
| ሲማድ . . . . . . . . . . . . . . | የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች |
| ECES . . . . . . . . . . . . . . | አውሮፓ የምርጫ ድጋፍ ማዕከል |
| EDF. . . . . . . . . . . . . . . | የኤርትራ መከላከያ ኃይሎች |
| ኢህአዴግ. . . . . . . . . . . . | የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር |
| ኤፊዲሪ . . . . . . . . . . . . | የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |
| ኤን ዲ አይ . . . . . . . . . . . | ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም |
| ምርጫ ቦርድ . . . . . . . . . . | የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ |
| ደቡብ ብ/ብ/ህ/ ክልል . . . . . . | የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል |
| ሕ.ወ.ሓ.ት. . . . . . . . . . . . | ሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ |
| ዩኤስ ኤ አይ ዲ . . . . . . . . . | የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ |

# ምስጋና

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) በቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት ጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታዎችን እንዲሁም የመራጮች ምዝገባ ሂደቶችን የታዘቡ 91 የቅድመ-ህዝበ ውሳኔ ታዛቢዎችን፣ በሕዝበ ውሳኔ ቀን የተሰማሩ 434 ተቀማጭ እና 76 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች እንዲሁም በድህረ-ሕዝበ ውሳኔ ወቅት የተሰማሩ 50 የድህረ ሕዝበ ውሳኔ ታዛቢዎች በበጎ-ፈቃደኝነት ስሜት ላሳዩት ከፍተኛ ተነሳሽነት ሊያመሰግን ይወዳል። በተጨማሪም ኅብረቱ ለዋና አሰልጣኞች እና በሕዝበ ውሳኔ መረጃ ማዕከል ሲሰሩ ለነበሩ ለ20 የመረጃ ሰራተኞች ዕውቅናን ይሰጣል።

ይህ በእንዲህ አንዳለ ኅብረት ለምርጫ በዚህ ፕሮጀክት የተሳካ ይህንን ውጤት እንዲያገኝ በማስተባበር እና ማስፈጸም ላይ ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ኅብረቱን በበላይነት ለሚመራው ቦርድ፣ ለዋና ዳይሬክተሩ አቶ አበራ ኃይለማርያም፣ ብንያም አባተ፣ ኢዩኤል ዘለዓለም፣ ይስሐቅ አበባየሁ እና ሌሎች የኅብረት ለምርጫ ሰራተኞች፣ ምስጋና ያቀርባል። በተጨማሪም በታዛቢዎች ምልመላ ላይ ለተሳተፉት የኅብረት ለምርጫ አባል ድርጅቶች ምስጋና ሊያቀርብ ይወዳል።.

ኅብረት ለምርጫ የደቡብ ኢትዮጵያን ሕዝበ-ውሳኔ ትዝብት በተሳካ ሁኔታ ሊጠናቀቅ የቻለው የዴንማርክ ኤምባሲ እና አየርላንድ ኤምባሲ በአውሮፓ የምርጫ ድጋፍ ማዕከል ባደረጉት የገንዘብ ድጋፍ በመሆኑ ለእነዚህ ተቋማት ላቅ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል። በተጨማሪም ኅብረቱ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (ዩኤስ ኤ አይ ዲ) በበብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም በኩል ለቀረበለት የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ምስጋናው ከፍ ያለ ነው ።

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ)

# ዋና ማጠቃለያ

## ገለፃ

በኢፌዲሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 47 (2) በአንቀጽ 47 (1) በተዘረዘሩት ክልሎች ውስጥ የተካተቱት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የራሳቸውን ክልል የመመሥረት መብት ክልል የመመሥረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ እና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፣ ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤትም ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፣ ክልል የመመሥረት ጥያቄው ሕዝበ ውሳኔውን ባካሄደው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ በአብላጫ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ፣ እና የክልሉ ምክር ቤት የክልልነት ጥያቄ ላቀረበው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሥልጣን ሲያስረክብ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ከተሟሉ በሕዝበ ውሳኔው የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አባል እንደሚሆን ሕገ መንግሥቱ ይደነግጋል።

ባለፉት አራት አመታት ውስጥ የደቡብ ክልል ሶስት የክልልነት ህዝበ ውሳኔዎች የተካሄዱ ሲሆን ይህ ስድስት ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች ያካሄዱት ሕዝበ- ውሳኔ ሶስተኛው ነው። የደቡብ ክልል በ2012 ዓ.ም የሲዳማ ሕዝበ-ውሳኔን፣ በ2014 ዓ.ም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ሕዝበ-ውሳኔን ማስተናገዱ የሚታወስ ነው። የስድስቱ ዞኖች እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች የክልልነት ጥያቄ ለፌዴሬሽን ምክርቤት የቀረበው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ-ውሳኔ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ላይ የሚነሱ የክልልነት ጥያቄዎችን መፍትሄ እንዲያፈላጉ የተሾሙ የሰላም አምባሳደሮች[1] ባደረጉት አነሳሽነት እና የስድስቱ ዞኖች እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች ምክር ቤቶች ለፌደሬሽን ምክርቤት ባቀረቡት ማመልከቻ መሰረተ ነው። የፌደሬሽን ምክር ቤት የቀረበለትን ጥያቄ ተቀብሎ አጸድቆ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሕዝበ-ውሳኔውን እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ ማስተላለፉን ተከትሎ ሕዝበ- ውሳኔው ተግባራዊ ሆኗል።

ኅብረት ለምርጫም በደቡብ ክልል ለሶስተኛ ጊዜ የተካሄደውን የሕዝበ-ውሳኔ ወሳኝ ሂደቶችን ማለትም የቅድመ- ሕዝበ ውሳኔን፣ የሕዝበ-ውሳኔ ምርጫ ቀንን እንዲሁም ድህረ-ሕዝበ ውሳኔን ታዝቧል። በተጨማሪም በወላይታ ዞን የተካሄደውን የደጋሚ ህዝበ ውሳኔ ሂደት ታዝቧል። በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ በትዝብት ሥራው የደረሰባቸውን አንኳር ግኝቶች በሚከተለው ክፍል ይዳስሳል።

## የግኝቶች ማጠቃለያ

### በቅድመ-ሕዝበ  ውሳኔው የፖለቲካ ምህዳር እና የመራጮች ምዝገባ ሂደት

የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የመራጮች ትምህርት፣ ቅስቀሳ እንዲሁም የአጠቃላይ የሲቪክ ምህዳርን ታዝበዋል።

- ምንም እንኳን ታዛቢዎች በሲቪል ማህበራት መልማይነት የቀረቡ ቢሆንም የሲቪል ማህበራቱ በነበረባቸው የቴክኒክ እና የገንዘብ አቅም እጥረት ምክኒያት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ታዛቢዎችን ለገጠራማ አካባቢዎች ተደራሽ ማድረግ አዳጋች ሆኖ ነበር፤
- በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አማካኝነት ለመራጮች የተሰጠው ለሁለት ወራት ብቻ የቆየው ትምህርትን ከጊዜ አንፃር በሁሉም አካባቢዎች ለማዳረስ በቂ አልነበረም፤

1 Ethiopia Insight. (2020, October 10). Splitting the Southern Nations region into four can promote peace. Retrieved from https://www.ethiopia-insight.com/2020/10/10/splitting-southern-nations-region-into-four-can-promote-peace/

- ሕዝበ-ውሳኔው ሲካሄድ ሁለት አማራጮች የነበሩት ሲሆን ምልክቶቹም 'ነጭ እርግብ' እና 'ጎጆ' ነበሩ። ነገር ግን እነዚህ ሁለት አማራጮች በቅስቀሳ ወቅት በእኩል ደረጃ ለሕዝብ አልቀረቡም፤
- 10% የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ በምርጫ ቦርድ፣ ወይም በሌሎች ባለድርሻ አካላት የተዘጋጁ ክርክሮች እንደነበሩ ገልጸዋል፤
- በጋሞ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ሶስት የኅብረቱ ታዛቢዎች በቅድመ-ሕዝበ ውሳኔው ሂደት ላይ ለእስራት ተዳርገው እንዳይታዘቡ ገደብ ተጥሎባቸው ነበር። እነዚህን ታዛቢዎች ለማስፈታ እና ወደ ጣቢያዎች እንዲመለሱ ለማድረግ የኅብረት ለምርጫ ጽ/ቤት ከፍተኛ ጥረቶችን አካሂዷል፤
- የመራጮች ምዝገባ ሂደቱ የተከናወነው ከሞላ ጎደል በሕግ አግባብ መሰረት የነበረ ቢሆንም በአንዳንድ ጣቢያዎች ሕገወጥ ድርጊቶች ተፈጽሟል። በ35 (8%) የምዝገባ ጣቢያዎች መራጮች የመታወቂያ ካርዳቸውን ቢያሳዩም እንዳይመርጡ ክልከላ ሲደረግባቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ በ24(5%) ጣቢያዎች ቢያንስ አንድ ወይም ከዛ በላይ ተመዝጋቢዎች ማንነታቸውን ሳያረጋግጡ መዝግበዋል። በ22(5%) ጣቢያዎች ደግሞ አንዳንድ መራጮች የነዋሪነት ማረጋገጫ (መታውቂያ) ማቅረብ አልቻሉም ነበር፤
- የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የመራጮች ምዝገባን የሚያስፈጽሙ አካል ጉዳተኞችን እንዳልተመለከቱ የገለጹ ሲሆን ከሴቶች ተሳትፎ አኳያ ትዝብት ከተደረገባቸው 438 ጣቢያዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ የምዝገባ አስፈፃሚ ሴት መሆኗን ሪፖርት አድርገዋል።

# የሕዝበ-ውሳኔ ቀን ሂደት

- ለሕዝበ-ውሳኔ ትዝብት ኅብረት ለምርጫ 510 (434 ተቀማጭ እና 76 ተንቀሳቃሽ) ታዛቢዎችን አሰማርቷል። ከታዛቢዎች ዕውቅና አሰጣጥ መዘግየት፣ ከቦርዱ ለታዛቢዎች በተሰጡ አንዳንድ ባጆች ላይ የስሞች እና የፎቶግራፍ መደበላለቅ እንዲሁም እንዳይታዘብ ከተከለከለ አንድ ታዛቢ ውጪ ሌሎች የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸው ነበር፤
- የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በአንፃራዊነት በሕዝበ-ውሳኔው ቀን የነበሩ ሂደቶች የተከናወኑት የምርጫ ሕግ እና መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት መሆኑን ቢገልጹም አንዳንድ ጣቢያዎች በተከለከሉ ቦታዎች እንደተከፈቱ እና የምርጫ ቅስቀሳ ሥራዎች በጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ውስጥ ሲከናወኑ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፤
- ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አከፋፈት ጋር በሚመለከት በ362 (88%) ጣቢያዎች ድምጽ የመስጠት ሂደት የጀመረው ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ ነበር። ሆኖም ግን በ48(12%) ጣቢያዎች ሂደቱ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ቀድሞ ተጀምሯል። በምርጫ ሕጉ ድምጽ መስጠት መጀመር ያለበት ከጠዋቱ 12 ሰዓት ላይ እንደሆነ ተቀምጧል፤
- በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው 410 (100%) ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመራጮች ከማደላቸው በፊት ምልክት እንዳደረጉባቸው ታዛቢዎች ገልጸዋል። በተጨማሪም የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ሊታይ በሚችል ቦታ መቀመጣቸውን ገልጸዋል፤
- የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ሂደቶች በአብዛኛው ከቦርዱ መመሪያ ጋር በተስማማ መልኩ የተከናወኑ ቢሆንም በ6 (1%) ጣቢያዎች ፍቃድ የሌላቸው ግለሰቦች ሕጉ ከሚፈቅደው ውጪ በድምጽ አሰጣጡ ሂደት ውስጥ ተገኝተው ነበር። እነዚህ አሳሳቢ ሁነቶች ከስር በዝርዝር ተቀምጠዋል፤
- ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች መካከል በ14 (3%) ጣቢያዎች ውስጥ በአማካኝ 5 ሰዎች በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው ሳይኖር የመረጡ ሲሆን በ52 (12%) ጣቢያዎች ከ1-10 መራጮች ከመምረጣቸው በፊት በማይለቅ የጣት ቀለም ምልክት አልተደረገባቸውም፤
- በ398 (97%) ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጥራዊነት ቀኑን በሙሉ የተጠበቀ ሲሆን በ12(3%) ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጥራዊነት አልተጠበቀም ነበር።

# የድህረ-ሕዝበ ውሳኔ

በድህረ-ሕዝበ ውሳኔ ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመከታተል ኅብረት ለምርጫ 50 ታዛቢዎችን በማሰማራት ጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታዎችን፣ የሕዝብ አስተያየትን እንንዲሁም የሲቪክ ምህዳሩን ታዝቧል። በጠቅላላው በድህረ ሕዝበ-ውሳኔ ሂደት ውስጥ ምንም አይነት የተቃውሞ ሰልፎች፣ አድማ ወይም ግጭት አለመኖራቸውን እንዲሁም በመሰብሰብ እና በመንቀሳቀስ መብቶች እና ነፃነቶች ላይ የተጣሉ ክልከላዎች ወይም ገደቦች የታዩ ባይሆንም በሕዝበ ውሳኔው ውጤት ላይ ግን ከፍተኛ ጥርጣሬ በሕዝብ እንዳለ ተገልጿል።

# ዋና ዋና ምክረ-ሃሳቦች

- ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለመራጮች ትምህርት በቂ ጊዜን መስጠት አለበት። በተጨማሪም የመራጮች ትምህርትን የሚሰጡ የሲቪል ማህበራት እንዲበራከቱ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል። ምንም እንኳን ቦርዱ ለሶስት ድርጅቶች ድጋፍ ያደረገ ቢሆንም ኅብረት ለምርጫ ይህን ድጋፍ በቂ ሆኖ አላገኘውም። ተያይዞም የዓለም አቀፍ አጋሮች ለሥነ-ዜጋ እና መራጮች ትምህርት በቂ የሆነ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።
- በሲቪል ማህበራት ድርጅቶች፣ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲሁም በሚዲያዎች የተዘጋጁ ክርክሮች ጥቂት ነበሩ። በመሆኑም የሲቪል ማህበራት፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲሁም ሚዲያዎች የምርጫ ክርክሮችን በማዘጋጀት ረገድ ሚናቸውን በተባበረ እና በተሻለ መንገድ ሊወጡ ይገባል።
- በሕዝበ ውሳኔ ወቅት የሚደረጉ ክርክሮች የሕዝበ-ውሳኔውን አማራጮችን በሚገባ ሊያሳዩ ይገባል።
- በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ዕውቅና ባገኙና ኅብረት ለምርጫ ባሰማራቸው ታዛቢዎች እና በምርጫ ቦርድ ሠራተኞች እንቅስቃሴዎች ላይ ገደብ የመጣል ጥቂት ሁኔታዎች ተስተውለዋል፤ ይህም የሆነው ከአካባቢው የአስተዳደር አካላት የግንዛቤ ማነስ መሆኑን ኅብረት ለምርጫ ለመረዳት ችሏል። መሰል ገደቦችን ለመከላከል ምርጫ ቦርድ የአካባቢ አስተዳደር ኃላፊዎችን ግንዛቤ በማሳደግ በምርጫ ሂደት ገንቢ ሚናን እንዲጫወቱ ማድረግ አለበት።
- መራጮች ማንነታቸውን እና ነዋሪነታቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ሳያቀርቡ ሲመዘገቡ የነበሩ ሲሆን አስፈፃሚዎች መራጮችን ከህግ አግባብ ውጪ በቤት ለቤት ዘመቻ ሲመዘግቡ እንደነበርም ለመታዘብ ተችሏል። ይህንን ተከትሎም ምርጫ ቦርድ በ24 ጣቢያዎች የተከናወኑ የመራጮች ምዝገባ ሂደቶችን ሰርዟል። ይህን ታሳቢ በማድረግ ቦርዱ የምርጫ አስፈጻሚዎችን አቅም፣ የፖለቲካ ገለልተኛነት እና የስራ ነፃነት ሊያጤን ይገባል። ይህንን ጭምሮ ሌሎች ተያያዥ ችግሮችን ለማስቀረት ቦርዱ የአስፈፃሚዎችን አቅም፣ የፖለቲካ ገለልተኛነት እና ነፃነት በማጤን የምልመላ ሂደቱን ሊያከናውን ይገባል።
- ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈፃሚ ሆነው የሚቀጠሩ ሰራተኞችን ስልጠና ጥራት በማጠናከር የምርጫ ሕጉ በተጠበቀ መልኩ እንቅስቃሴዎችን እንደሚያደረጉ ማረጋገጥ አለበት። ይህን በማድረግ በምርጫ ሕጉ እና መመሪያው የተደነገጉ በመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ መስጫ ቀን የሚካሄዱ ወሳኝ ኹነቶች በምርጫ ህጉ መሰረት መከናወናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። በሕዝበ-ውሳኔ ከማይሳተፉ አካባቢዎች አስፈፃሚዎችን የመመልመል አማራጭን ቢመለከት የተሻለ ይሆናል።

# መግቢያ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ ከ175 በላይ አባል የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን ያቀፈ አገር-በቀል ድርጅት ነው። ኅብረት ለምርጫ ከፖለቲካ ወገንተኝነትና ተፅዕኖ ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ የታዛቢ ቡድን ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረጉ ምርጫዎች አካታች፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት የሰፈነባቸው እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት ለማድረግ የተቋቋመ ድርጅት ነው።

ኅብረት ለምርጫ በግንቦት 2012 ዓ.ም ሶስት ዋና ዋና አላማዎችን አንግቦ የተመሰረተ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው። እነዚህም ዓላማዎች፡- አባል ድርጅቶች በመራጮች እና የዜግነት ትምህርት እንዲሳተፉ የአቅም ማጎልበት ሥራዎችን ለመስራትና የዜጎችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ፣ አባል ድርጅቶች በምርጫ ትዝብት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ድጋፍ ማድረግ እና ከምርጫ ሂደቶች ጋር የተገናኙ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀት፣ በማሰናዳት እና ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ ናቸው። ኅብረት ለምርጫ በሁሉም የትዝብት እንቅስቃሴዎቹ ሶስት-ሂደት ያለው የምርጫ ትዝብት መንገድ ይከተላል እነዚህም ሂደቶች የቅድመ-ምርጫ፣ የምርጫ ቀን እና ድህረ-ምርጫ ሂደቶች ናቸው።

ኅብረት ለምርጫ በ2012 ዓ.ም የተካሄደውን የሲዳማ ሕዝበ-ውሳኔ፣ ስድስተኛውን ጠቅላላ ምርጫ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ሕዝበ-ውሳኔን ታዝቧል። ኅብረቱ የሚያከናውናቸው ተግባራት በምርጫ ትዝብት ላይ ብቻ የተወሰኑ ሳይሆኑ ከምርጫ ጋር ተቀራራቢነት ባላቸው እንደ የመራጮች ትምህርት እና ምርጫን ተከትሎ የሚዲያ ዘገባ ክትትል የሚመለከቱ ናቸው። ከስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ በመቀጠል ኅብረት ለምርጫ የአባላቱን አቅም የማጎልበት፣ በምርጫ ሥርዓት ሪፎርም እና በአካታች የፖለቲካ ሂደቶች ላይ ሲሰራ ቆይቷል።

ኅብረት ለምርጫ ስልታዊ የሆነ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም የምርጫ ትዝብት ዘዴን ይከተላል። ይህ ሪፖርትም ኅብረት ለምርጫ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በሚገኙ ስድስት ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም በተካሄደው የሕዝበ-ውሳኔ ላይ እንዲሁም በሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በወላይታ ዞን በተካሄደው የድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ ላይ ባካሄደው ትዝብት ላይ መሰረት ያደረገ ነው። ሪፖርቱ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያ ክፍል በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም በስድስቱ ዞኖች እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች በተካሄደው የሕዝበ-ውሳኔ ሂደት የኅብረቱ የትዝብት ግኝት ላይ ያተኩራል። የሪፖርቱ ሁለተኛ ክፍል፣ በሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም በወላይታ ዞን በተካሄደው የድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ የትዝብት ግኝቶችን ይዳስሳል።

01

# ክፍል አንድ
# ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄደው የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት



Image: NEBE

# ምዕራፍ 1: ሕዝበ -ውሳኔው የተካሄደበት የፖለቲካ አውድ

## በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል የሚነሱ የክልልነት ጥያቄዎች

የደቡብ ኢትዮጵያ ሪፈረንደም በኢትዮጵያ ደ/ብ/ብ/ህ ክልል ውስጥ ከተደረጉ ሕዝበ-ውሳኔዎች (ሲዳማ ክልል እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል) ውስጥ አንዱ ነው። በክልሉ እየጨመረ የመጣውን የክልልነት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሠላም አምባሳደሮች ኮሚቴ ከሕዝብ እና ከልሂቃን ጋር እንዲመካከር እና የመፍትሄ ሃሳብ እንዲያቀርብ ኃላፊነት ተሰጥቶት የነበረ ሲሆን የሠላም ቡድኑ የመፍትሄ ሃሳቦችን የያዘ ሪፖርት ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ ክልል ለሚገኙ የዞን እና የልዩ ወረዳ ኃላፊዎች በጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ በሰኔ 02 ቀን 2014 ዓ.ም አቅርቦ ነበር። የመፍትሄ ሃሳቡ የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልልን ለሶስት መከፈልን ያካተተ ሲሆን እነዚህም ክፍሎች ኦሞቲክ፣ ማዕከላዊ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የተባሉ ክልሎች ናቸው።

ሆኖም ግን የክልሉን በክላስተር አደረጃጀት መከፋፈል ከወላይታ እና ከጉራጌ ዞኖች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል። የወላይታ የዞን ምክር ቤት የወላይታን የክልልነት ጥያቄ በታህሳስ ቀን 2011 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ማጽደቁ የሚታወስ ሲሆን[2] ይህ የክልልነት ጥያቄ መጠነ ሰፊ ተቃውሞዎችን ጨምሮ በግንቦት 2011 በተካሄደው የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢህዴን) የ10 ቀን የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አድማ መመታቱ ማሳያ ነው።[3]

በተመሳሳይ መልኩ የጉራጌ ዞን ምክር ቤት መንግስት ያቀረበውን ምክረ ሃሳብ ተቃውሞታል።[4] ከዚህም በተጨማሪ የዞኑ ነዋሪዎች የጉራጌ ዞን ዋና ከተማ በሆነችው ወልቂጤ ከተማ አድማ በመምታት የመንግስት እና የንግድ እንድቅስቃሴ ሥራዎችን በማቆም ተቃውሟቸውን ገልጸዋል።[5] በሌላ በኩል የፌደሬሽን ምክር ቤት በወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ኮንሶ፣ ጌድዮ ዞኖች እና ደራሼ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ አሌ እና ባስኬቶ ልዩ ወረዳዎች በአንድ ክልል ለመደራጀት በየምክር ቤቶቻቸው ያጸደቁትን ውሳኔ በሃምሌ ወር 2014 ዓ.ም አጽድቋል።[6] ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ፌደሬሽን ምክር ቤት አዲስ ክልል ለማደራጀት የሕዝበ-ውሳኔ ምርጫ እንዲደረግ ወስኗል። በመቀጠልም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሕዝበ-ውሳኔ እንዲያዘጋጅ እና ለፌደሬሽን ምክር ቤት ውጤቱን እንዲያሳውቅ ትዕዛዝ ተላልፎለታል።[7]

በዚህም መሰረት ቦርዱ በስድስቱ ዞኖች እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ሕዝበ-ውሳኔ አካሂዷል። በሕዝበ-ውሳኔው የቀረቡት አማራጮች ሁለት ሲሆኑ የመጀመሪያው አማራጭ 'በነጭ እርግብ' ምስል የተወከለው "ስድስቱ ዞኖች እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች በአንድ ክልል እንዲደራጁ እደግፋለሁ" የሚል ሲሆን ሁለተኛው አማራጭ በሌላ በኩል 'በጎጆ' ምስል የተወከለ ሲሆን የሚያቀርበው አማራጭ ደግሞ "የአዲሱን ክልል ምስረታ አለመደገፍን" ወክሎ ቀርቧል። በዚህ ላይ የተለያዩ ትችቶች የተሰነዘሩ ሲሆን የቀረቡት የሕዝበ ውሳኔ አማራጮች የመራጮችን ፍላጎት በትክክል የወከሉ መሆናቸው ላይ ጥያቄዎችን አስነስቷል። ተያይዞም የአዲሱን ክልል መደራጀት የማይደግፉ መራጮች ቁጥር በልጦ ቢገኝ ምን አይነት ውጤት ይኖረዋል ለሚሉ ትችቶች ተጋልጧል።

2 FESSHA, Yonatan. "Internal Secession and Federalism in Ethiopia." IACL-IADC Blog, 15 July 2019, https://blog-iacl-aidc.org/2019-posts/2019/7/15/internal-secession-and-federalism-in-ethiopia.
3 FESSHA, Yonatan. "Internal Secession and Federalism in Ethiopia." IACL-IADC Blog, 15 July 2019, https://blog-iacl-aidc.org/2019-posts/2019/7/15/internal-secession-and-federalism-in-ethiopia.
4 Addis Standard. "News update: Gurage Zone Council declines new cluster restructuring, stick to earlier request." 11 August 2022, https://addisstandard.com/news-update-gurage-zone-council-declines-new-cluster-restructuring-stick-to-earlier-request/.
5 Addis Standard. "News update: Gurage Zone Council declines new cluster restructuring, stick to earlier request." 11 August 2022, https://addisstandard.com/news-update-gurage-zone-council-declines-new-cluster-restructuring-stick-to-earlier-request/.
6 Addis Standard Breaking: Six zones and five special woredas to hold a referendum August 18,2022 https://addisstandard.com/breaking-six-zones-and-five-special-woredas-to-hold-a-referendum/
7 Addis Standard Breaking: Six zones and five special woredas to hold a referendum August 18,2022 https://addisstandard.com/breaking-six-zones-and-five-special-woredas-to-hold-a-referendum/

## የፖለቲካ አውድ

በሰሜን ኢትዮጵያ ከሁለት ዓመታት በላይ በቆየው ግጭት ከ600 ሺህ በላይ ህይወት አጥፍቶ[8]፣ ሚሊየኖችን የእርዳታ ፈላጊ አድርጎ በጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም[9] በፌደራል መንግስቱ እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ(ሕ.ወ.ሓ.ት.) መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተፈረመው የሠላም ስምምነት ተጠናቋል።[10] የፕሪቶሪያው የሠላም ስምምነት በሕዳር 3 ቀን 2015 ዓ.ም በተደረገው የናይሮቢ ስምምነት ተጠናክሯል። ይህንንም ተከትሎ የኤርትራ መከላከያ ኃይሎች ከትግራይ ክልል መውጣት መጀመራቸውን እንዲሁም የሕወሓት ሃይሎች ከባድ የጦር መሳሪያዎችን ለፌደራል መከላከከያ ማስረከብ በመጀመራቸው በክልሉ ለረዥም ጊዜ ተቋርጠው የነበሩ የባንክ፣ መብራት፣ ውሃ እንዲሁም የአየር በረራ ትራንስፖርት የመሳሰሉ መሰረታዊ አገልግሎቶች መመለስ እንዲሁም ባልተጠበቀ መልኩ የሕወሓት አመራሮች እና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ በጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም መገናኘታቸው ተስተውሏል። በሌላ በኩል በኦሮሚያ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች የሚገኙ ታጣቂ ቡድኖች የክልል መንግስታቱን መገዳደራቸውን ቀጥለዋል። በኢትዮጵያ ሲካሄድ በቆየው መጠነ-ሰፊ ግጭት ንጹሃን ዜጎች ግንባር ቀደም የገፈቱ ቀማሽ ከመሆናቸውም በላይ የግጭት ኢላማ ሆነዋል።[11]

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሶስት ሊቃነ ጳጳሳት የኦሮሚያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ መመስረታቸውን እንዲሁም 26 ፓትሪያርኮችን በኦሮሚያ ክልል መሾማቸውን ካወጁ በኋላ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ባሉ አባቶች መካከል የተፈጠረው መከፋፈል የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ሆኖም ግን ወር ከፈጀ ምክክር እና ውይይት በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ እና 'ተለይተናል' ያሉት ሊቃነ-ጳጳሳት በቤተ-ክርስቲያኒቱ ቀኖና መሰረት መስማማታቸውን ለሕዝብ ገልጸዋል።[12]

# ምዕራፍ 2: የሕዝበ-ውሳኔ ምርጫ እና የምርጫ ትዝብት የሕግ ማዕቀፍ

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት

የ1987 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት ሕብረ-ብሔራዊ የመንግስት ስርዓትን ለመተግበር በማለም ለብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የራስን በራስ የማስተዳደር መብት እንዲሁም በማንኛውም ጊዜ የራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል።[13] በዚህም መሰረት የሕገመንግስቱ አንቀጽ 47(2) በአንቀጽ 47(1) ላይ የተዘረዘሩ የፌደራል መንግስት አባላት ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራሳቸውን ክልል የመመሥረት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ክልል የመመስረት መብት ተፈፃሚ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች በተመለከተ ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 47 ንዑስ 3 የሚከተሉብትን ዝርዝር መስፈርቶች እና ሂደቶችን ያስቀምጣል፡-

8 Ethiopia sets out on long road to peace after two years of war Tommy Wilkes https://www.reuters.com/world/africa/ethiopia-sets-out-long-road-peace-after-two-years-war-2023-01-05/
9 Ethiopia's Bumpy Road To Lessons From the Western Balkans https://www.iipvienna.com/new-blog/2023/1/23/ethiopias-bumpy-road-to-peace-and-lessons-from-the-western-balkans
10 Ethiopia's Bumpy Road To Lessons From the Western Balkans https://www.iipvienna.com/new-blog/2023/1/23/ethiopias-bumpy-road-to-peace-and-lessons-from-the-western-balkans
11 Raleigh, Clionadh. "Multiple Complications Threaten to Result in a Dangerous Re-escalation." ACLED, 2022, https://acleddata.com/10-conflicts-to-worry-about-in-2022/ethiopia/mid-year-update/.
12 Addis Standard. "News Analysis: Ethiopian Orthodox Church leaders resolve schism through dialogue, restore Church unity "based on church's canon"." February 16, 2023, https://addisstandard.com/news-analysis-ethiopian-orthodox-church-leaders-resolve-schism-through-dialogue-restore-church-unity-based-on-churchs-canon/.
13 Berhe, M. G., & Gebresilassie, F. H. (2021). Nationalism and self-determination in contemporary Ethiopia. Nations and Nationalism, 27, 96-111. https://doi.org/10.1111/nana.12647BERHEANDGEBRESILASSIE111

- “ክልል የመመሥረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፤
- ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፣ ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤትም ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፤
- ክልል የመመሥረት ጥያቄው ሕዝበ ውሳኔውን ባካሄደው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ በአብላጫ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ፤ እና
- የክልሉ ምክር ቤት የክልልነት ጥያቄ ላቀረበው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሥልጣን ሲያስረክብ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ከተሟሉ በሕዝበ ውሳኔው የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አባል እንደሚሆን ሕገ መንግሥቱ ይደነግጋል።”[14]

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክርቤትን ለማጠናከር፣ ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 251/1993

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የብሔር፣ ብሔረሰቦች ወይም ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በተመለከተ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን እንዳለው፤ ከዚህ አንፃርም ማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ወይም ሕዝብ “ማንነቴ አልታወቀልኝም፣ ራስን በራስ የማስተዳደር መብቴ ተሸርሽሯል፣ ቋንቋዬን፣ ባሕሌንና ታሪኬን የማሳድግበት ሁኔታ አልተመቻቸልኝም …”[15] የሚል ዕምነት ካደረበት ተዋረዱን ጠብቆ ጥያቄውን ለምክር ቤቱ ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል።[16] በተለይም የአዋጁ አንቀፅ 19 (3) የማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ክልል የመመሥረት ጥያቄ ለማቅረብ ከዚህ በታች ያሉትን መስፈርቶች

- “የክልል መመሥረት ጥያቄው በብሔር፣ ብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛው ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፣
- ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፤
- ክልል የመመሥረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ በሚካሄድ ሕዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ፤
- የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ፣
- በሕዝበ ውሳኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢፌዴሪ አባል ሲሆን በሥራ ላይ እንደሚውል ይደነግጋል።”[17]

አዋጁ በአንቀጽ 19 (3) (2) በዚህ አንቀጽ ንዑሥ ቁ (1) (ለ)በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክልል የመመሥረት ጥያቄ አልተፈጸመልኝም ወይም በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ጥያቄውን ለምክር ቤቱ ማቅረብ እንደሚችል ሲደነግግ ጥያቄው ለምክር ቤቱ የሚቀርበው በጽሑፍ ሆኖ የክልል ምሥረታ ጥያቄ ባቀረበው የብሔር፣ ብሔረሰቡ ምክር ቤት መሆኑን ፤ምክር ቤቱም በቀረበለት ጉዳዮች ላይ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚሰጥ አዋጁ ይደነግጋል።

14 Proclamation No. 1/1995 Proclamation to Pronounce the Coming into Effect of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia. Article 39. Available at: https://chilot.me/2013/11/proclamation-no-1-1995-proclamation-to-pronounce-the-coming-into-effect-of-the-constitution-of-the-federal-democratic-republic-of-ethiopia/. accessed 19, July, 2023
15 Proclamation No. 251/2001 Consolidation of the House of the Federation and the Definition of its Powers and Responsibilities Proclamation Article 19(1)
16 Ibid
17 Proclamation No. 251/2001 Consolidation of the House of the Federation and the Definition of its Powers and Responsibilities Proclamation Article 19(3)

# የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2012

የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2019 ዓ.ም በኢትዮጵያ ከሚካሄዱ የምርጫ ዓይነቶች መካከል ህዝበ-ውሳኔ አንዱ መሆኑን ደንግጓል። አዋጁ ህዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ ከወሰነው አካል ጋር በመመካከር ቦርዱ ህዝበ ውሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ህዝበ ውሳኔውን እንደሚያከናውን፤ በንኡስ ቁጥር 3 ቦርዱ በህገመንግሥቱ ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጋር በመመካከር ድምጽ የሚሰጥበትን ቀን፤ በህዝበ ውሳኔው በድምጽ ሰጪነት ለመሳተፍ መሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ የሚሠፍረው ለውሳኔ የቀረበው አማራጭ አጻጻፍ እና የህዝበ ውሳኔውን አስመልክተው የሚደረጉ የቅስቀሳ ዓይነቶችን ይዘት እንደሚወስን ይህም በሚወጣ መመሪያ ዝርዝር አፈጻጸሙ እንደሚወስን ይደነግጋል። የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2012 ዓ.ም ስለ ምርጫ ታዛቢዎች በተለይም የምርጫ ሂደትን ለመታዘብ የሚፈልጉ የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ለቦርዱ በማመልከትና ሲፈቀድላቸው የሚሰጣቸውን የታዛቢነት የምስክር ወረቀት በመያዝ ምርጫ ለመታዘብ መቻላቸውን እንዲሁም ምርጫውን ለመታዘብ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው የምርጫ ታዛቢዎች በቦርዱ የሚዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የሥነ ምግባር መመሪያ መቀበላቸውን በድርጅቶቹና በወኪሎቻቸው ፊርማ ማረጋገጥ እንደሚኖርባቸው ይደነግጋል። ቦርዱ ከአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎችን ምርጫ ለመታዘብ ጥያቄ ሲቀርብለት:-

- ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት ህጋዊ ሰውነት ያለው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት መሆኑን፤
- የድርጅቱ የቦርድ አባላት እና መሪዎች ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻና ለትርፍ ያልተቋቋመ፤ የማንኛውም መንግሥታዊ ተቋም አካል አለመሆኑን፤
- የሚያሰማራቸው ግለሰቦች ምርጫን በገለልተኝነት ለመታዘብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን በማጣራት የሥነ ምግባር ደንብ መቀበላቸውን ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም የታዛቢነት ሰርተፊኬት እንደሚሰጥ አዋጁ ይደነግጋል።

ቦርዱ "በአዋጁ የተደነገጉት መስፈርቶች አልተሟሉም" በሚል ምክንያት የቀረበለትን የታዛቢነት ማመልከቻ ያልተቀበለ እንደሆነ ውሳኔውን ማመልከቻውን በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ የማሳወቅ ግዴታን በቦርዱ ላይ አዋጁ ይጥልበታል። አመልካቹ በቦርዱ ውሳኔ ካልተስማማ በ14 ቀን ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲታይለት አቤቱታውን ሊያቀርብ እንደሚችል አዋጁ ይደነግጋል። ማንኛውም የምርጫ ታዛቢ ከሥነ ምግባር ደንቡና ከገባው ግዴታ ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደ አግባብነቱ የተፈጸመውን ስህተት ጠቅሶ ለግለሰቡና ለወከለው ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከስህተቱ እንዲታረም ለማዘዝ አልያም ግለሰቡ ወይም ወካዩ ድርጅት ከታዛቢነት ለማገድ እንደሚችል አዋጁ ይደነግጋል። የምርጫ ታዛቢዎችን መብት በተመለከተም የምርጫ ታዛቢነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው የድርጅት ወኪል በምርጫ ጣቢያዎች በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቆ የማግኘት፤ የምርጫ ሰነዶችን የመመልከት፣ የድምጽ አሰጣጥ እና የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን የመታዘብ፤ የታዘቧቸውን ወይም ያጋጠሟቸውን ጉድለቶች ለቦርዱ ጽህፈት ቤት የማቅረብ መብት እንዳላቸው አዋጁ ይደነግጋል። አዋጁ የምርጫ ታዛቢነት የምስክር ወረቀት ከቦርዱ ያገኘ የምርጫ ታዛቢ የታዛቢነት መታወቂያውን የመያዝና ሲጠየቅ የማሳየት፤ የምርጫ አስፈፃሚዎች የሚሰጡትን መመሪያ የማክበር፤ የምርጫው ሂደት በትክክልና በብቃት እንዳይካሄድ ከሚያደናቅፍ ተግባር የመቆጠብ፤ ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት በአዋጁ ተደንግጓል።

# ምዕራፍ 3 ፥ የትዝብት ዘዴ

ምርጫ ከአንድ ቀን የዘለለ የተለያዩ ጉዳዮችን ያቀፈ ሂደት ነው። ኅብረት ለምርጫ በጥር 2015 ዓ.ም የተካሄደውን ሕዝበ-ውሳኔ የታዘበው ይህን ምርጫን እንደ ሂደት መመልከት በሚለው መርሁ ነው። በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል በሚገኙ 6 ዞኖች እና 5 ልዩ ወረዳዎች የተካሄደውን ሕዝበ-ውሳኔ የቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ፣ የሕዝበ-ውሳኔን ቀን እና የድህረ-ሕዝበ ውሳኔ ሂደቶችን ታዝቧል። ይህም የሕዝበ-ውሳኔውን አካታችነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት መገምገምን እንደዋነኛው ዓላማው አድርጎ ነው። በተጨማሪም የትዝብት ሥራው ስልታዊ እና ተዓማኒ በተሞላበት መንገድ መረጃን በመሰብሰብ ለሕዝብ ይፋ ማድረግን እንደዓላማ ይዞ ተነስቷል። ኅብረት ለምርጫ በሕዝበ ውሳኔ ትዝብቱ በሥራ ላይ ያዋለው የታዛቢዎች ስምሪት ዘዴ ከስር ተቀምጧል።

| ዞን/ልዩ ወረዳ | የቅድመ-ሕዝበውሳኔ ታዛቢዎች | የሕዝበ-ውሳኔ ቀን ታዛቢዎች | የድህረ ሕዝበ-ውሳኔ ታዛቢዎች |
|---|---|---|---|
| አሌ | 2 | 4 | 1 |
| አማሮ | 2 | 11 | 1 |
| ቡርጂ | 1 | 5 | 1 |
| ባስኬቶ | 2 | 6 | 1 |
| ደራሼ | 1 | 10 | 1 |
| ኮንሶ | 3 | 14 | 2 |
| ወላይታ | 29 | 143 | 15 |
| ጋሞ | 21 | 74 | 9 |
| ጎፋ | 9 | 36 | 4 |
| ጌዲዮ | 14 | 92 | 10 |
| ደቡብ ኦሞ | 7 | 39 | 5 |
| **ጠቅላላ** | **91** | **434** | **50** |


# የቅድመ -ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት

# የረዥም ጊዜ ትዝብት

ኅብረት ለምርጫ የሕዝበ-ውሳኔው ቀን ከመድረሱ በፊት ከሕዳር 22 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ጥር 23 2015 ዓ.ም ያለውን ጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታ የሚታዘቡ 91 የረዥም ጊዜ ታዛቢዎችን ሕዝበ-ውሳኔው በሚካሄድባቸው አካባቢዎች አሰማርቷል። ኅብረት ለምርጫ እነዚህን 91 የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች ከአባል ድርጅቶቹ በመመልመል፣ በማሰልጠን እና በማሰማራት የቅድመ ሕዝበ-ውሳኔ ሂደቱን ተዓማኒነት፣ ግልጽነት እና አካታችነት በመታዘብ የዜጎችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማበረታታት ታዝቧል። ኅብረት ለምርጫ ተመጣጣኝ የትዝብት ዘዴን የተከተለ ሲሆን በዚህ ዘዴ መሰረት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሕዝበ-ውሳኔው በሚካሄድባቸው ዞኖች እና ልዩ ወረዳዎች በሚያቋቁማቸው ጣቢያዎች ብዛት ላይ መሰረት በማድረግ ታዛቢዎችን የሚመለምል፣ የሚያሰለጥን እና የሚያሰማራ ይሆናል።

## የመራጮች ምዝገባ

ከጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታ በተጨማሪም ኅብረት ለምርጫ ያሰማራቸው 91 የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች ከታህሳስ 11 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 26፣ 2015 ዓ.ም የተካሄደው የመራጮች ምዝገባ ሂደት ታዝበዋል። በዚህም እያንዳንዱ የኅብረት ለምርጫ የቅድመ-ምርጫ ታዛቢ 6 የምዝገባ ጣቢያዎችን በመታዘብ ሪፖርት አድርጓል።






ሁሉም የቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ ታዛቢዎች ከሕዝበ ውሳኔው በፊት ያሉ የፖለቲካ እና የመራጮች ምዝገባ ሂደቶች ጋር የተገናኙ መረጃዎችን በገለልተኝነት እንዲሰበስቡ እና ቀድመው በተዘጋጁ ስታንዳርድ ቅጾች ሪፖርት እንዲያደርጉ የሚያስችላቸውን ስልጠና ተሰጥቷቸዋል።

# ሕዝበ-ውሳኔ ቀን

## የመስክ ትዝብት

በሕዝበ ውሳኔ ቀን ኅብረት ለምርጫ በስድስቱም ዞኖች እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች ታዛቢዎችን መልምሎ፣ አሰልጥኖ አሰማርቷል። በዚህም ሂደት ሁለት ተመጋጋቢ ታዛቢዎችን የተከተለ ሲሆን እነዚህም ተንቀሳቃሽ እና ተቀማጭ ታዛቢዎች ናቸው። ኅብረት ለምርጫ በአጠቃላይ 510 ታዛቢዎችን ያሰማራ ሲሆን ከነዚህም መካከል 76 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በአመቺነት (Convenient Observers deployment methodology) አሰማርቷል። እያንዳንዱ ተንቀሳቃሽ ታዛቢ 5 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን እንዲታዘብ ተደርጓል። የተቀሩትን 434 ተቀማጭ ታዛቢዎች ሲሆኑ እነዚህን ታዛቢዎች በተመጣጣኝ የታዛቢዎች ስርጭት ዘዴ (Proportional Observers deployment methodology) ለማሰማራት ጥረት አድርጓል። ሆኖም ግን ይህን ተመጣጣኝ ዘዴ አንዳንድ ታዛቢዎች ከትዝብት ሥራው በመውጣታቸው አማካኝነት ሙሉ በሙሉ ለመተግበር አልቻለም። የኅብረቱ ታዛቢዎች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከንጋቱ 11:30 ተገኝተው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን አከፋፈት እና ዝግጅት እንዲታዘቡ ተደርጓል። ከዚህ ባለፈም በድምጽ መስጫው ቀን በተገኙበት የድምጽ መስጫ ጣቢያ ቀኑን ሙሉ በመዋል የድምጽ አሰጣጥ፣ የድምጽ መስጫ ጣቢያ መከፈት እና መዘጋት፣ እንዲሁም የድምጽ ቆጠራን እንዲታዘቡ ለማድረግ ተችሏል።







## የመረጃ ማዕከል

ኅብረት ለምርጫ በዞኖቹ እና ልዩ ወረዳዎቹ ከተሰማሩ ታዛቢዎቹ የሚደርሱትን መረጃዎች ተዓማኒነት፣ እርግጠኝነት እና ጥራት ለማረጋገጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመረጃ ማዕከል መስርቷል። ይህ የመረጃ ማዕከል 20 የመረጃ ሠራተኞችን የያዘ ሲሆን የተቋቋመበት ዋነኛው ዓላማም ከታዛቢዎች የሚመጡ መረጃዎችን ለማደራጀት፣ ለማጣራት እንዲሁም ለመተንተን አግዟል።

# የድህረ-ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት

ከሕዝበ ውሳኔ ቀን በኋላ ኅብረት ለምርጫ 50 የድህረ-ሕዝበ ውሳኔ ታዛቢዎችን በማሰማራት ጠቅላላ የፖለቲካ ሂደቱን፣ በሕዝበ-ውሳኔው ውጤት ላይ ያለውን የማህበረሰብ ምልከታ እንዲሁም የሲቪክ ምህዳሩን ታዝበዋል። እነዚህ ታዛቢዎች የትዝብት ግኝቶቻቸውን በሳምንት ሁለት ቀናት (ሰኞ እና አርብ) ለአራት ሳምንታት ከጥር 30 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ የካቲት 25 ቀን 2015 ዓ.ም ሪፖርት አድርገዋል።



# ምዕራፍ 4 ፧ የትዝብት ግኝቶች

## ሀ) የቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት ግኝቶች

ከታች የተዘረዘሩት ግኝቶች ኅብረት ለምርጫ ከሕዳር 22 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ጥር 23 ቀን 2015 ዓ.ም. በረዥም ጊዜ ታዛቢዎች የሰበሰባቸውን መረጃዎችን ያካተተ ነው። እነዚህ ታዛቢዎች ጠቅላላ የቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ ሁኔታውን እና የመራጮች ምዝገባ ሂደቱን ቀድመው የተዘጋጁ የትዝብት ቅጾችን በመጠቀም ታዝበው ሪፖርት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ኅብረቱ ከላይ በተጠቀሰው የግዜ ገደብ ውስጥ የነበረውን ጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታ የዳሰሱ አጠቃላይ 456 ሪፖርቶችን እንዲሁም ከታህሳስ 11 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄደው የመራጮች ምዝገባን የተመለከቱ 438 ሪፖርቶችን ሰብስቧል።

### ከሕዝበ-ውሳኔ በፊት የነበረው አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ

### የመራጮች ትምህርት

በኢትዮጵያ የመራጮች ትምህርትን መስጠት የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቀዳሚ ኃላፊነት ነው። አዋጅ ቁጥር 1133/2019 አንቀጽ 7(2) ቦርዱ የመራጮችን ትምህርት እንዲያከናውን እንዲሁም የመራጮች ትምህርትን ለሚያከናውኑ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ፍቃድ የመስጠት፣ የመከታተል እና የመቆጣጠር ኃላፊነቶች ተሰጥተውታል።[18] በዚህም መሰረት ቦርዱ የመራጮች ትምህርትን የመስጠት ፍላጎት ላላቸው የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ማመልከቻቸውን እንዲያስገቡ ጥሪ አድርጎ ነበር።[19] ይህን ጥሪ ተከትሎ ቦርዱ ለ16 የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በሕዝበ-ውሳኔው የመራጮች ትምህርትን እንዲሰጡ ፍቃድ ሰጥቷል።[20]

ኅብረት ለምርጫ ከሕዝበ-ውሳኔው በፊት ያለውን ጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታ ትዝብት ጋር በተገናኘ ሕዝበ-ውሳኔው በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የመራጮች ትምህርት መኖር አለመኖሩን፣ የመራጮች ትምህርት ሲሰጥ የነበረበትን መንገድ፣ ተደራሽነት እንዲሁም ገጥመው የነበሩ ተግዳሮቶችን ለማየት ሞክሯል። ከስር ያለው ዝርዝር ኅብረት ለምርጫ ከሕዝበ-ውሳኔው በፊት ያለውን ጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታ ከዳሰሱ ታዛቢዎች በተላኩ 555 ሪፖርቶች ላይ መሰረት ያደረገ ነው።

***የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ***

- 468 (84%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎችን መታዘባቸውን ሲገልጹ 87(16%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች ግን በአካባቢያቸው ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎችን አለመታዘባቸውን ገልጸዋል። ከነዚህ መካከል በብዛት ማለትም ከ87 ሪፖርቶች ውስጥ 50 (58%) የሚሆኑት ሪፖርት የተደረጉት በጌድዮ ዞን ከሚገኙ ታዛቢዎች ነው።
- 370 (67%) ከታዛቢዎች የመጡ ሪፖርቶች የተካሄዱ የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሁለቱንም ጾታዎች፣ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን እና አካል ጉዳተኞችን ያሳተፈ መሆኑን የገለጹ ሲሆን 185 (33%) ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎች አካታች እንዳልነበሩ ጠቅሰዋል።
- ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹን የመራጮች ትምህርት ጥራትን እንዲገመግሙ የጠየቀ ሲሆን በዚህም መሰረት ከ555 ሪፖርቶች ውስጥ በአማካይ "ከበቂ በታች" ብለው አስቀምጠዋል።

---

18 Article 7(2) of proclamation 1133/2019


19 በደ/ብ/ብ/ህዝቦች ክልል 6 ዞኖች እና 5 ልዩ ወረዳዎች ህዝበ ውሳኔ ዙሪያ የመራጮች ትምህርት መስጠት ለሚፈልጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የቀረበ ጥሪ, የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ. Available at: https://nebe.org.et/am/node/796 (Accessed: February 27, 2023).

20 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በሚገኙ ስድስት ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች ላይ ለሚካሄደው ሕዝበ ውሣኔ የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት በቦርዱ ፈቃድ የተሰጣቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች, የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ. Available at: https://nebe.org.et/am/node/804 (Accessed: February 27, 2023).

## የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ

የመራጮች ትምህርት የሚሰጥበት መንገድ እጅግ ወሳኝነት አለው። ይህን በማመን ኅብረት ለምርጫ በደቡብ ኢትዮጵያ በተካሄደው ሕዝበ-ውሳኔ በጥቅም ላይ የዋሉ የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ መንገዶች የትኞቹ እንደሆኑ ለመለየት ጥረት አድርጓል። በዚህም መሰረት የመራጮች ትምህርት የገጽ ለገጽ፣ የቢል ቦርድ፣ የሕትመት፣ የመንገድ ላይ ትርዒቶች፣ የአካባቢ ሚዲያ (ራዲዮ እና ቴሌቪዥን)፣ ማህበራዊ ሚዲያ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘዴዎችን በመጠቀም ሲሰጥ እንደነበር ለመታዘብ ችሏል።
በዚህም መሰረት

- 186 (34%) ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት በገጽ ለገጽ ዘዴን በመጠቀም እንደተሰጡ፣ 34 (6%) ሪፖርቶች ደግሞ ሲሰጥ የነበረው የመራጮች ትምህርት አካባቢያዊ ሚዲያዎችን (ራዲዮ እና ቴሌቪዥን) በመጠቀም እንደነበር እንዲሁም 25(5%) ሪፖርቶች ደግሞ የመራጮች ትምህርት የተሰጠው በማህበራዊ ሚዲያ እና ሌሎች የቴክኖሎጂ መንገዶችን ተጠቅመው መሆኑን ያሳያሉ። ይበል በሚያሰኝ መልኩ 193(35%) ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት ከአንድ በላይ የስርጭት ዘዴን በመከተል ሲሰጥ እንደነበር ጠቁመዋል።





## የመራጮች ትምህርት ተደራሽነት

- 329 (59%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት የመራጮች ትምህርት በገጠራማ አካባቢዎች በቀላሉ ተደራሽ እንደነበር ነው። ሆኖም ግን በጌዲዮ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ከሚገኙ ታዛቢዎች የመጡ ሪፖርቶች በእነዚህ አካባቢዎች የተደረጉ የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎች ዝቅተኛ የተደራሽነት መጠን እንደነበራቸው ያስረዳሉ። ከጌዲኦ ዞን የመጡ 13 (22%) ሪፖርቶች እንዲሁም ከደቡብ ኦሞ ዞን የተላኩ 23 ሪፖርቶች የተካሄዱ የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎች ዝቅተኛ የተደራሽነት ደረጃ እንዳላቸው ጠቅሰዋል።

## በመራጮች ትምህርት ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

- የተሰበሰበው መረጃ በመራጮች ትምህርት ላይ ከተስተዋሉ ተግዳሮቶች ውስጥ ዋነኛው የገንዘብ እጥረት መሆኑን ያሳያል። 290 (53%) ሪፖርቶች ይህንኑ ያሳያሉ። በሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃ የተቀመጡት ተግዳሮቶች የመራጮች ትምህርትን የሰጡ ድርጅቶች የፕሮጀክት አመራር ድክመት 93(17%) ሪፖርቶች እንዲሁም የሶስተኛ ወገኖች ጣልቃ ገብነት እንደሆነ 24(4%) ሪፖርቶች ያሳያሉ።




## የህዝበ ውሳኔ ቅስቀሳ እና ክርክሮች

በሕዝበ ውሳኔ ወቅት የሚደረጉ የቅስቀሳ እንቅስቃሴዎች የሕዝበ ውሳኔ አማራጮችን ለመራጮች በማስተዋወቅ እንዲሁም በማስረዳት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በመሆኑም ፍትሃዊ፣ ተደራሽ እና እኩል የሆነ የቅስቀሳ ምህዳር መኖሩ ለአጠቃላይ የምርጫ ሂደት አስፈላጊ ነው። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ-ውሳኔ ወቅት ያለውን የቅስቀሳ ሁኔታ ከጅምሩ አንስተው፣ የቅስቀሳ ሥራዎች ምን ያህል ተደራሽ እና በእኩል መጠን ሁለቱንም አማራጮች ለመራጮች ያሳዩ ናቸው የሚለውን እንዲታዘቡ ተጠይቀዋል።

በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ-ውሳኔ ወቅት ሁለት የሕዝበ-ውሳኔ አማራጮች ቀርበዋል። በዚህም መሰረት አንደኛው አማራጭ የተወከለው "ነጭ እርግብ" ሲሆን የሚወክለውም ስድስቱ ዞኖች እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች በአንድ አዲስ ክልል እንዲደራጁ ሲሆን ሌላኛው አማራጭ ደግሞ "ጎጆ" ምልክት ሲሆን ይህም ስድስቱ ዞኖች እና አምስቱ ልዩ ወረዳዎች በነባሩ ደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ስር እንዲቆዩ የሚደግፍ ነው።

**ለሕዝበ-ውሳኔው የቀረቡ አማራጮች**



የ6ቱ ዞኖች **(ኮንሶ፣ ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጋሞ፣ ጌዴኦ፣ ጎፋ)** እና የ5ቱ ልዩ ወረዳዎች **(ቡርጂ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ አማሮ፣ ዴራሼ)** በአንድ የጋራ ክልል መደራጀትን እደግፋለሁ።



የ6ቱ ዞኖች **(ኮንሶ፣ ወላይታ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጋሞ፣ ጌዴኦ፣ ጎፋ)** እና የ5ቱ ልዩ ወረዳዎች **(ቡርጂ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ አማሮ፣ ዴራሼ)** በአንድ የጋራ ክልል መደራጀትን አልደግፍም።

የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ከቅስቀሳ ሥራዎች ጋር የተያያዙ የሚከተሉትን ግኝቶች መታዘባቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

- 433 (78%) ሪፖርቶች የቅስቀሳ ሥራዎች ሲከናወኑ እንደነበር ጠቁመዋል። በተጨማሪም 275 (50%) ሪፖርቶች ሲከናወኑ የነበሩ የቅስቀሳ ሥራዎች ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዳልነበሩ ገልጸዋል።
- 54(10%) ሪፖርቶች በምርጫ ቦርድ ወይም በተመዘገቡ የሲቪል ማህበር ድርጅቶች የተዘጋጁ የሕዝበ-ውሳኔው ክርክሮች ከአንድ ጊዜ በላይ ሲደረጉ መታዘባቸውን ገልጸዋል። እነዚህ ክርክሮች መደረጋቸውን ሪፖርት ያደረጉ በወላታ፣ ቡርጂ፣ጋሞ፣ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ እና አማሮ የሚገኙ ታዛቢዎች ናቸው።
- ሁሉም ሪፖርቶች ሲደረጉ የነበሩት ቅስቀሳዎች ሁለቱንም የሕዝበ ውሳኔ አማራጮች ያላሳዩ እንደውም ሁሉም ሊባል በሚቻል መልኩ አንደኛውን አማራጭ ማለትም የ"ነጭ እርግብ" አማራጭን የደረጉ ቅስቀሳዎች በስፋት ሲደረጉ እንደነበር ለመታዘብ ተችሏል።
- 528 (95%) ከታዛቢዎች የመጡ ሪፖርቶች በሕዝበ ውሳኔው ወቅት ግጭቶች፣ ረብሻዎች፣ የተዛቡ መረጃዎች፣ የጥላቻ ንግግሮች እንዳልነበሩ የገለጹ ሲሆን በሌላ በኩል በ26 (5%) ሪፖርቶች ታዛቢዎች ምንም እንዳላዩ ገልጸዋል።

## የሲቪክ ምህዳር

የሲቪል ማህበር ድርጅቶችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም ሌሎች ቡድኖችን ያካተተ አመቺ የሲቪክ ምህደር ለምርጫ ሂደት እጅግ አስፈላጊ ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግ የኅብረት ለምርጫ የቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት አመቺ የሲቪክ ምህዳር መኖር አለመኖሩን በማጣራት በሲቪል ማህበራት፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ጋዜጠኞች እና የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ላይ የደረሱ ክልከላዎች ወይንም የሙብት ጥሰቶችን በተመለከተ ትዝብት አድርጓል።

በሕዝበ ውሳኔ ሂደት ውስጥ የነበረውን የሲቭክ ምህዳር በተመለከተ ኅብረት ለምርጫ የሚከተሉትን ግኝቶች ላይ ለመድረስ ችሏል፦


- ሁሉም 555 (100%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች በሕዝበ-ውሳኔው ወቅት በሚዲያ ሠራተኞች እና ጋዜጠኞች ላይ የተስተዋለ እስራት፣ ማስፈራራት ወይም ግድያ አለመኖራቸውን ገልፀዋል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፎን በተመለከተ በደቡብ ኦሞ ዞን የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች በቅስቀሳ ሥራዎች እንዳይሳተፉ ጫና እንደተደረገባቸው ገልጸዋል።
- በሲቪል ማህበር ድርጅቶች ላይ የሚደረግ ክልከላ እና ገደብን በተመለከተ ኅብረት ለምርጫ ሶስት ሪፖርቶች ደርሰውታል። እነዚህ ሪፖርቶች ከጋሞ ዞን ( በደረማሎ ወረዳ በደረሱ ሁለት ሁኔታዎች) እና  በደቡብ ኦሞ ባጋጠመ አንድ ሁኔታ (በናጸማይ ቀበሌ) ላይ የተደረጉ ሪፖርቶች ናቸው። በነዚህ አጋጣሚዎች፣ የዞን አስተዳዳሪዎች እና የአካባቢ ፖሊሶች ከምርጫ ቦርድ ፍቃድ አግኝተው የተሰማሩ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በየምርጫ ጣቢያዎች ተንቀሳቅሰው እንዳይታዘቡ ክልከላ አድርገዋል። እነዚህ የአካባቢው የአስተዳደር ኃላፊዎች ምርጫ ቦርድ የሰጣቸውን የታዛቢዎች የዕውቅና ሰነዶች ሕጋዊነት እንደማይቀበሉ ገልጸው ከፌደራል፣ ከክልል እና ከዞን አስተዳደሮች ተጨማሪ መረጃዎችን እንደሚፈልጉ በመግለጽ ታዛቢዎችን በእስር ሊያቆዩ ችለዋል። ይህ መረጃ የደረሰው ኅብረት ለምርጫ ከቦርዱ ኃላፊዎች ጋር በመተባበት የታሰሩ ታዛቢዎች እንዲፈቱ ሊያደርግ ችሏል።
- በምርጫ ቦርድ እንቅስቃሴዎች ላይ የተደረጉ ክልከላዎችን በተመለከተ በደራሼ ልዩ ወረዳ የሚገኙ የአካባቢ መዋቅር ኃላፊዎች የቦርዱን ሠራተኞች በአካባቢው የምርጫ ቁሳቁሶችን እንዳያደርሱ መከልከላቸውን ገልጸዋል።
- የሲቪል ማህበር ድርጅቶች በሕዝበ ውሳኔው የተጫወቱትን ሚና በተመለከተ

1. ***ተሳትፎ***: 307 (55%) ሪፖርቶች ሲቪል ማህበር ድርጅቶች በሕዝበ ውሳኔው ቁልፍ ሚና መጫወታቸውን ገልጸዋል። የሲቪል ማህበር ድርጅቶች አነስተኛ ሚና እንደተጫወቱ ሪፖርት የተደረገባቸው አካባቢዎች በአማሮ እና ኮንሶ ዞኖች ሲሆን በእነዚህ አካባቢዎች ከ60% በላይ የታዛቢዎች ሪፖርቶች በአካባቢያቸው ምንም አይነት የሲቪል ማህበራት እንቅስቃሴ አለመታዘባቸውን ገልጸዋል።
2. ***ተደራሽነት***: 310 (56%) ሪፖርቶች በሕዝበ ውሳኔው የነበሩ የሲቪል ማህበራት እንቅስቃሴዎች በገጠራማ አካባቢዎች ተደራሽ እንዳልነበሩ ገልጸዋል።

# የመራጮች ምዝገባ

የምርጫ ቦርድ በስድስቱ ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች የሚገኙ መራጮችን ምዝገባ ከታህሳስ 11 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ባሉት ቀናት አከናውኗል።  በምዝገባ ወቅት በወላይታ እና ጎፋ ዞኖች በሚገኙ 10 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ባጋጠሙ የሕግ ጥሰቶች ቦርዱ የመራጮች ምዝገባውን መሰረዙን አሳውቋል።[21] የመራጮች ምዝገባን ለማከናወን የምርጫ ቦርድ በአጠቃላይ 3,769 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን ያቋቋመ ሲሆን 3,028,770 ዜጎች ለመምረጥ ተመዝገባዋል። ከተመዘገቡ መራጮች ውስጥ 493 (296 ወንዶች እና 197 ሴቶች) መራጮች አካል ጉዳተኞች ናቸው። የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር በጾታ ሲከፋፈል 1,575,371 ወንዶች፣ 1,453,399 ሴቶች) ናቸው።[22]

21 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሕዝበ ውሣኔ በሚካሄድባቸው አንዳንድ ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የተፈጸሙ የሕግ ጥሠቶችን በተመለከተ የወሰዳቸው የዕርምት ዕርምጃዎች, የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ. Available at: https://nebe.org.et/am/node/825 (Accessed: March 3, 2023).
22 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግሥት ሥር በሚገኙ ስድስት ዞኖችና አምስት ልዩ ወረዳዎች ላይ የሚያካሂደውን ሕዝበ ውሣኔ የመራጮች መዝገብ ለሕዝብ ዕይታ ክፍት አደረገ,  የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ. Available at: https://nebe.org.et/am/node/843  (Accessed: March 3, 2023).




ኅብረት ለምርጫ የሕዝበ ውሳኔውን የመራጮች ምዝገባ ለመታዘብ 76 ታዛቢዎችን ከታህሳስ 11 ቀን ፣ 2015 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም አሰማርቷል። በመቀጠል የተዘረዘሩት ግኝቶች ከ438 የምዝገባ ጣቢያዎች የበተገኙ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

የመራጮች ምዝገባ ትዝብትን በተመለከተ ኅብረት ለምርጫ ምዝገባው ከአገር አቀፍ እንዲሁም በአህጉር እና በአለም አቀፍ ደረጃ በተቀመጡ መለኪያዎች መሰረት መከናወን ወይም አለመከናወናቸውን ለመታዘብ አቅዶ ተነስቷል።

## የምዝገባ ጣቢያዎች አደረጃጀት እና ተደራሽነት

በምርጫ አዋጁ መሰረት የመራጮች ምዝገባ መከናወን የሚችለው በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ ነው። የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት እና ተደራሽነት የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን በምርጫ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ እንዲሁም የመራጮች ምዝገባ ሂደቱን ግልጽነት ለማረጋገጥ ወሳኝነት አለው። ኅብረት ለምርጫ የመራጮች ምዝገባ ሂደት ትዝብት የምዝገባ ጣቢያዎችን አደረጃጀት እና ተደራሽነት የቃኘ ነበር። ኅብረት ለምርጫ የመራጮች ምዝገባ እንዲታዘቡ ከተሰማሩ ታዛቢዎች በተገኙ ሪፖርቶች መሰረት የሚከተሉትን ግኝቶች ላይ ደርሷል፦

- ኅብረት ለምርጫ የታዘባቸው 400 (96%) የምዝገባ ጣቢያዎች በቀላሉ ተደራሽ የነበሩ ቢሆንም 16 (4%) ጣቢያዎች በመካከለኛ የተደራሽነት ደረጃ ላይ ተገኝተዋል።
- ትዝብት የተደረገባቸው የምዝገባ ጣቢያዎች የተቋቋሙባቸውን ቦታዎች በተመለከተ፤ 254 (58%) ጣቢያዎች በከተማ አካባቢዎች የተቋቋሙ ሲሆን 101 (23%) ጣቢያዎች ግን በከፊል ከተሜ አካባቢዎች እንዲሁም 83(19%) ጣቢያዎች ደግሞ በገጠራማ አካባቢዎች የተቋቋሙ ናቸው።
- በ192 (44%) የምዝገባ ጣቢያዎች የተቋቋሙት በሕንፃዎች ውስጥ ሲሆን 54(12%) ጣቢያዎች በድንኳኖች ውስጥ እንዲሁም 192 (44%) ጣቢያዎች በሌሎች ሕንፃ ወይንም ድንኳን ባልሆኑ ቦታዎች ተቋቁመዋል።
- በ52 (12%) ጣቢያዎች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው አካል ጉዳተኞች ወይንም የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው አዛውንቶች፣ ሕፃናትን የያዙ እናቶች ወይም ሌሎች) ያለድጋፍ ወደ ምዝገባ ጣቢያዎች በቀላሉ መግባት አልቻሉም ነበር።
- በምርጫ ቦርድ መመሪያዎች መሰረት የምዝገባ ጣቢያዎች የፀሀይ እና የዝናብ ሽፋን እንዲሚያስፈልጋቸው ቢገልጹም 230(53%) የምዝገባ ጣቢያዎች ምንም አይነት የፀሐይ እና የዝናብ መከላከያ አልነበራቸውም።
- ከምርጫ ሕጉ በተቃራኒ፣ በፖለቲካ ፓርቲ ሕንፃዎች (የጣቢያ ቁጥራቸው 790601364505 እና 790601364502 የሆኑ 2 ጣቢያዎች) እንዲሁም በግል መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የጣቢያ ቁጥራቸው 790704141703 እና 790501128402 የሆኑ 2 ጣቢያዎች) ውስጥ የተከፈቱ የምዝገባ ጣቢያዎች እንደነበሩ ለመታዘብ ተችሏል።

## የምርጫ አስፈፃሚዎች

የምርጫ ሕጉ አንቀጽ 15(9) ቦርዱ በሚያከናውናቸው እንቅስቃሴዎች “የጾታ ውክልናን ታሳቢ እንዲያደርግ” ይደነግጋል። መመሪያ ቁጥር 06/2021 የመራጮች ምዝገባ በሚካሄድባቸው ጣቢያዎች ከሚሰሩ አስፈፃሚዎች ውስጥ ቢያንስ አንድ ሴት አስፈፃሚ እንድትኖር ይደነግጋል። በዚህ መሰረት ኅብረት ለምርጫ ያሰማራቸው ታዛቢዎች እነዚህ ድንጋጌዎች በምዝገባ ጣቢያዎች ውስጥ ምን ያክል እንደተተገበሩ ታዝበዋል።

- ከቦርዱ መመሪያዎች ጋር በተስማማ መልኩ በአማካይ 3 የምዝገባ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ተግኝተው የነበረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዷ ሴት ነበረች፤
- የመራጮች ምዝገባ አስፈፃሚ በመሆን የተሳተፉ አካል ጉዳተኞን በተመለከተ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ምንም አይነት አካል ጉዳት ያለባቸውን የምርጫ አስፈፃሚዎችን እንዳላስተዋሉ ገልጸዋል።

## የመራጮች ምዝገባ ሕጎች እና ሂደቶች

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ምዝገባን ለማከናወን የተለያዩ ሕጎች እና ሂደቶችን ይጠቀማል። የምርጫ ሕጉ የመራጮች ምዝገባ ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ፣ በቤት ለቤት ምዝገባ አልያም በመንቀሳቀስ እንዳይከናወን ይከለክላል። በመራጮች የምዝገባ ሕግ መሰረት የመራጮች ምዝገባ በመንግስት የስራ ሰዓት እንደሚከናወን አስቀምጧል። በተጨማሪም ድምጽ ለመስጠት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ማንነታቸውን፣ ዕድሜያቸውን እና መኖሪያ አድራሻቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።

- ከመራጮች ምዝገብ መመሪያ ጋር በተስማማ መልኩ በአብዛኞቹ የምዝገባ ጣቢያዎች ማለትም በ437 ወይም 99.7% ጣቢያዎች ምዝገባ የተጀመረው ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡30 ነበር። በጋሞ ዞን በሚገኝ 1 የምዝገባ ጣቢያ የምዝገባ ሂደቱ እስከ ቀኑ 6፡30 አልተጀመረም ነበር። በዚህ ጣቢያ ይህ ሊሆን የቻለው የጣቢያ አስፈፃሚዎች የመራጮች ምዝገባ መራጮች ቤተክርስቲያን በሚሄዱበት እሁድ ቀን እንደማይከናወን በማሰባቸው እንደሆነ ተገልጿል።
- የምርጫ ሕጉ የምዝገባ ሂደቱ በጊዜያዊነት ለ1 ሰዓት የምሳ እረፍት ሊቋረጥ እንደሚችል ይደነግጋል። በአብዛኛው ጣቢያዎች (429 ወይም 98%) የምዝገባ ሂደቱ አልተቋረጠም ነበር። በተጨማሪም በ9 (2%) የምዝገባ ጣቢያዎች ሂደቱ ሕጉ ከሚፈቅደው የ1 ሰዓት የምሳ ዕረፍት ውጪ ከ30 ደቂቃ በላይ ተቋርጦ ነበር። እነዚህ 9 የምዝገባ ጣቢያዎች የሚገኙት በወላይታ ዞን (2 ጣቢያዎች)፣ አሌ ልዩ ወረዳ (4 ጣቢያዎች)፣ ጌዲዮ ዞን (2 ጣቢያዎች) እና ኦሞ ዞን (1 ጣቢያ) ነው።
- በምርጫ ሕጉ መሰረት የመራጮች ምዝገባ የሚከናወነው ለመመዝገብ ፍላጎት ያላቸው መራጮች ማንነታቸውን እና መኖሪያቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ሲያቀርቡ ነው። በዚህ መሰረት ኅብረት ለምርጫ የሚከተሉት ግኝቶች ላይ ደርሷል፡-
- የምርጫ ሕጉ ከሚገልጸው ውጪ በ35(8%) ጣቢያዎች አስፈላጊውን ሰንዶች ያመጡ ዜጎች እንዳይመዘገቡ ተከልክለዋል። እነዚህ ሪፖርቶች በወላይታ ዞን (19 ጣቢያዎች) ቡርጂ ልዩ ወረዳ (4 ጣቢያዎች)፣ ኮንሶ ዞን (2 ጣቢያዎች)፣ ጎፋ ዞን (1 ጣቢያ)፣ ጋሞ ዞን (3 ጣቢያዎች) እና ደቡብ ኦሞ ዞን (6 ጣቢያዎች)።

1. ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች ውስጥ 24 (5%) ጣቢያዎች ውስጥ መራጮች ማንነታቸውን ሳያረጋግጡ ሲመዘገቡ ነበር። እነዚህ ጣቢያዎች የሚገኙት በኮንሶ ዞን (1 ጣቢያ)፣ በወላይታ ዞን (8 ጣቢያዎች) ፣ በጋሞ ዞን (6 ጣቢያዎች)፣ በጌዲዮ ዞን (5 ጣቢያዎች) ፣ ጎፋ ዞን (1 ጣቢያ)፣ በደቡብ ኦሞ ዞን (1 ጣቢያ) እና በቡርጂ ልዩ ወረዳ (2 ጣቢያዎች) ነው።
2. በ22 (5%) የምዝገባ ጣቢያዎች መራጮች የመኖሪያ አድራሻቸውን ሳያረጋግጥ ተመዝግበዋል። እነዚህ ጣቢያዎች በኮንሶ ዞን (1 ጣቢያ)፣ ወላይታ ዞን (8 ጣቢያዎች)፣ ጋሞ ዞን (9 ጣቢያዎች)፣ ጎፋ ዞን (2 ጣቢያዎች) እና ቡርጂ ልዩ ወረዳ (2 ጣቢያዎች) ይገኛሉ።

- ኅብረት ለምርጫ የጸጥታ አካላት በምዝገባ ጣቢያዎች መገኘታቸውን የታዘበ ሲሆን ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች ውስጥ በ209 (48%) ጣቢያዎች ውስጥ የጸጥታ አካላት ከጣቢያዎቹ ውጪ ተገኝተው ለምዝገባ ሂደቱ ጥበቃ ሲያከናውኑ አልነበረም።

## ለ) የሕዝበ ውሳኔ ቀን ድምጽ አሰጣጥ


በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ለተካሄደው ሕዝበ ውሳኔ ኅብረት ለምርጫ በጠቅላላ 434 ተቀማጭ ታዛቢዎችን አሰማርቷል። ሆኖም ግን በተለያዩ ተግዳሮቶች ምክንያቶች ኅብረት ለምርጫ ከ410 ተቀማጭ ታዛቢዎች ብቻ የተሟላ ሪፖርት ደርሶታል። የሚከተለው መረጃ ከ410 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከተሰበሰቡ ሪፖርቶች የተቀናበረ ነው።

#### የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አከፋፈት

በምርጫ ሕጉ መሰረ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የሚከፈቱት ከጠዋቱ 12 ሰዓት ሲሆን የሚዘጉት ደግሞ ከምሽቱ 12 ሰዓት ነው። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አዘገጃጀትን እንዲታዘቡ ከጠዋቱ 11:30 በየጣቢያዎቹ ደርሰዋል። ከስር ያሉት ግኝቶች ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አከፋፈት ጋር የተገናኙ ናቸው።

#### የድምጽ መስጠት መጀመር

- የድምጽ መስጫ ጣቢያ ኃላፊዎች በጣቢያዎች ከመከፈቻ ሰዓቱ ቀድመው ከጠዋቱ 12 ሰዓት ወደ ጣቢያዎች መድረስ አለባቸው። በ400 (98%) ጣቢያዎች ውስጥ አስፈፃሚዎች ከጠዋቱ 11:30 ደርሰው ነበር።
- በ409 (99%) ጣቢያዎች ታዛቢዎች ወደ ጣቢያዎች እንዲገቡ ፍቃድ ተሰቷቸው ነበር። ሆኖም በአንድ በጋሞ ዞን በሚገኝ ድምጽ መስጫ ጣቢያ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢ ወደ ምርጫ ጣቢያ እንዳይገባ ተከልክሎ የነበረ ሲሆን ይህ ታዛቢ ከቆይታ በኋላ በኅብረት ለምርጫ ጽ/ቤት ጥረት እንዲገባ ሊደረግ ችሏል።
- ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አከፋፈት ጋር በተገናኘ በ362 (88%) ጣቢያዎች ድምጽ የመስጠት ሂደት የጀመረው ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ ነበር። ሆኖም ግን በ48(12%) ጣቢያዎች ሂደቱ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ቀድሞ ተጀምሯል። በምርጫ ሕጉ ድምጽ መስጠት መጀመር ያለበት ከጠዋቱ 12 ሰዓት ላይ እንደሆነ ተቀምጧል።




ትዝብት በተደረገባቸው 407 (99%) ጣቢያዎች የተቋቋሙት በምርጫ ሕጉ በተፈቀዱ ቦታዎች ሲሆን ሕጉ ከሚፈቅደው ውጭ የተቋቋሙ ጥቂት ጣቢያዎችም ተስተውለዋል። ዝርዝሮቹ በአሳሳቢ ሁነቶች ክፍል ስር ተካተዋል።

### የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት

- የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ በምርጫ ማረጋገጥ በአለም አቀፍ ደረጃ የታወቀ መብት ነው። በመሆኑም የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም ሰዎች በተለይም የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው ሰዎች በቀላሉ ተደራሽ ሊሆኑ ይገባል። ሆኖም ግን ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች 17ቱ (4%) ለአካል ጉዳተኞች አመቺ አልነበሩም።

### የምርጫ ቁሳቁሶች መሟላት

- የውጤት ማመሳከሪያ ቅጽ ከሌለባቸው 4 ጣቢያዎች ውጪ በ410 ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ የምርጫ ቦርድ ሕጋዊ ማህተም፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን ማሸጊያ፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን እና የመራጮች መዝገብ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው ነበር።በተጨማሪም የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ከመታሸጋቸው በፊት ባዶ መሆናቸው ተረጋግጠው ነበር።

### የምርጫ አስፈፃሚዎች

- በአማካይ 4 የምርጫ አስፈፃሚዎች ትዝብት በተደረገባቸው 410 ጣቢያዎች ውስጥ የተገኙ ሲሆን ከነዚህ አስፈጻሚዎች ውስጥ 2 ሴቶች ነበሩ። በተጨማሪም በ93(23%) ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያ ኃላፊ የነበሩት ሴቶች ናቸው።


## የድምጽ አሰጣጥ ሂደት

### ቅድሚያ የተሰጣቸው መራጮች

- በ408 (99%) ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ አስፈፃሚዎች በሰልፍ ላይ ላሉ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአዛውንቶች፣ ለአቅመ ደከሞች፣ ለነፍሰጡር እንዲሁም ህፃናት ለያዙ ወላጆች መራጮች ቅድሚያ ሲሰጡ ነበር። ሆኖም ግን በተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች ትዝብት በተደረገባቸው 2(1%) ጣቢያዎች ከላይ ለተጠቀሱት መራጮች ቅድሚያ አልተሰጣቸውም ነበር። ድጋፍን በተመለከት በሁሉም 410 (100%) ጣቢያዎች አካል ጉዳተኛ መራጮች በግል ኢጋዦቻቸው ድጋፍ እንዲደረግላቸው ተደርጎ ነበር።

### ሕጋዊ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን መከተል

- በ358 (87%) ትዝብት የተደረገባቸው ጣቢያዎች ሁሉም መራጮች የማይለቅ የጣት ቀለም በጣታቸው ላይ ተደርጎላቸው የነበረ ሲሆን በ52 (12%) ጣቢያዎች ከ1-10 መራጮች ከመምረጣቸው በፊት በማይለቅ የጣት ቀለም ምልክት አልተደረገባቸውም ነበር። በ398 (97%) ጣቢያዎች  የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጥራዊነት ቀኑን ሙሉ የተጠበቀ ሲሆን በ12(3%) ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጥራዊነት አልተጠበቀም ነበር።
- ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች መካከል በ14 (3%) ጣቢያዎች ውስጥ በአማካኝ 5 ሰዎች በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው ሳይኖር መርጠዋል እንዲሁም በ6 (1%) ጣቢያዎች ፍቃድ የሌላቸው ግለሰቦች በድምጽ አሰጣጡ ሂደት ውስጥ ተገኝተው ነበር። እነዚህ አሳሳቢ ሁነቶች ከስር በዝርዝር ተቀምጠዋል። በ1 ጣቢያ የድምጽ መስጠት ሂደቱ ተቋርጦ ነበር።
- በሕጉ መሰረት የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የሚዘጉት ከምሽቱ በ12 ሰዓት እንደሆነ ተቀምጧል። በ11(3%) ጣቢያዎች በሕግ ከተቀመጠው የመዝጊያ ሰዓት ቀደም ብለው የተዘጉ ሲሆን 391 (95%) ጣብያዎች ደግሞ የተዘጉት ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ 1 ሰዓት ባለው ጊዜ ሲሆን 8(2%) ጣቢያዎች ከምሽቱ 1 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ መዘጋታቸውን ለማወቅ ተችሏል።




- በ139 (34%) ጣቢያዎች ውስጥ በሰልፍ ላይ የነበሩ ሁሉም መራጮች በመዝጊያው ሰዓት የምርጫ ሕጉ በሚያዘው መሰረት እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል። የምርጫ ሕጉ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዝጊያ ሰዓት በሰልፍ ላይ የሚገኙ መራጮች መምረጥ እንዲችሉ ይፈቅዳል።
- በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው 410 (100%) ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመራጮች ከማደላቸው በፊት ምልክት እንዳደረጉባቸው ገልጸዋል። በተጨማሪም የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ሊታይ በሚችል ቦታ መቀመጣቸውን ገልጸዋል።

**የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች**

- በ344 (84%) የጸጥታ አካላት ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውጪ በሁሉም ሰዓት ተገኝተው ነበር። በተጨማሪም በ57 (14%) ጣቢያዎች የጸጥታ አካላት ለተወሰኑ ሰዓታት ተገኝተው የነበረ ሲሆን በ9(2%) ጣቢያዎች በሁሉም ሰዓት ምንም አይነት የጸጥታ ሰራተኞች ከድምጽ መስጫ ጣቢያ ውጪ አልተገኙም ነበር።[23]

**የድምጽ ቆጠራ**

- ትዝብት በተደረገባቸው 375 (91%) ጣቢያዎች የውጤት ማመሳከሪያ ቅጾች ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውጭ ተለጥፈው ነበር። በተጨማሪም በሁሉም 410 (100%) ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራ በድምጽ መስጫው ቀን በጣቢያዎች ውስጥ ተከናውኗል። ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራ ሂደት የተቋረጠባቸው ሁኔታዎች እንዳልነበሩ ሪፖርት ተደርጓል። የድምጽ መስጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን በቆጠራ ወቅት ማሳየታቸውን እንዲሁም ኃላፊዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ተቀባይ መሆን አለመሆናቸው ለመወሰን ተመሳሳይ መስፈርቶችን ተጠቅመዋል።

# አሳሳቢ ሁነቶች

አሳሳቢ ሁነቶች ከፍተኛ የሆኑ ከምርጫ ሕግ ጋር የሚቃረኑ በምርጫ ሂደት የሚስተዋሉ ግድፈቶች ሲሆን እነዚህ ግድፈቶች በተፈጥሯቸው የምርጫ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖን ያሳድራሉ። ታዛቢዎች አሳሳቢ ኩነቶች በሚያጋጥማቸው ወቅት ወዲያውኑ የአሳሳቢ ሁነቶችን ለመላክ በተዘጋጁ መታዘቢያ ቅጾች በመሙላት ለኅብረት ለምርጫ የመረጃ ማዕከል እንዲልኩ ተነግሯቸው ነበር። በኅብረት ለምርጫ መረጃ ማዕከል የሚገኙ ሰራተኞች ሁነቶቹን የማጣራት እና የማረጋገጥ ሥራዎችን ያከናወኑ ሲሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን 24 አሳሳቢ ሁነቶችን አጣርተው አረጋግጠዋል።

23 በቡርጂ ልዩ፣ በወላይታ ዞን ዳሞት ሶሬ፣ በጋሞ ዞን ጨንቃ ወረዳ፣ ጌዲኦ ዞን ቡሌ ወረዳ፣ ጌዲኦ ዞን ዲላ ከተማ፣ ጎፋ ዞን አይዳ ልዩ፣ ወላይታ ዞን ቦዲቲ ከተማ በሚገኙ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በታዘቧቸው የምርጫ ጣቢያዎች የጸጥታ ኃላፊዎች አልተገኙም።

**ያልተሟሉ የምርጫ ቁሳቁሶች**

1. በአማሮ ልዩ ወረዳ (1 ጣቢያ) እና በጋሞ ዞን ከምባ ወረዳ (2 ጣቢያዎች) በሚገኙ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የመጡ ሪፖርቶች የውጤት ማመሳከሪያ ቅጾች እንዳልነበሩ አመላክተዋል።

**በተከለከሉ ቦታዎች የተከፈቱ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች**

2. ደቡብ ኦሞ ዞን ጂንካ ከተማ ጤና አዳም 1 የምርጫ ጣቢያ የምርጫ ሕጉ ከሚፈቅደው ውጭ በግለሰብ መኖሪያ ቤት እንደተከፈተ ተገልጿል።
3. በጌዲዮ ዞን በራዳ መንደር የሚገኘው ገልማ 02 ጣቢያ በሕግ በተከለከለ የመዝናኛ ቦታ መከፈቱን ለመረዳት ተችሏል።

**ፍቃድ የሌላቸው ግለሰቦች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ መግባት**

4. በጋሞ ዞን ገራሴ ወረዳ የሚገኘው ማናውዴ ገራሴ 01 ጣቢያ ውስጥ ፍቃድ አስተባባሪ ነን የሚሉ ሠዎች ፍቃድ ሳይኖራቸው ወደ ጣቢያው ውስጥ መግባታቸውን ተረጋግጧል።
5. በጎፋ ዞን ሳውላ ከተማ የሚገኘው ቁለቲ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ውስጥ ፍቃድ የሌላቸው ግለሰቦች ሰንደቅ ዓላማ ለመስቀል ወደ ጣቢያው ውስጥ ገብተው ነበር።
6. በደቡብ ኦሞ ዞን ቱርሚ ከተማ በሚገኘው ኮላቴጋ ጣቢያ ፍቃድ የሌላቸው ግለሰቦች ፎቶ ግራፍ ለማንሳት ወደ ጣቢያው ገብተዋል።
7. በጌዲዮ ዞን ገደብ ወረዳ በሚገኘው ሞኮኒሳ ጣቢያ የወረዳ አስተዳዳሪዎች በድምጽ ቆጠራ ወቅት መገኘታቸውን ለመታዘብ ተችሏል።
8. በጎፋ ዞን ሳውላ ከተማ በሚገኝ ገልማ 02 ጣቢያ ውስጥ የብልጽግና ፓርቲ አባላት በድምጽ መስጠት ሂደት ውስጥ መገኘታቸውን ለማወቅ ተችሏል።
9. በጋሞ ዞን ከምባ ዙሪያ ወረዳ በሚገኘው ባኬ ጣቢያ ውስጥ ሁለት ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች (አንድ ወንድ እና አንድ ሴት) የታዛቢነት መታወቂያቸውን ወይም ሌላ ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ሳያቀርቡ እንደታዛቢ ወደጣቢያው ገብተው ነበር።

**በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ውስጥ የቅስቀሳ ተግባራትን ማከናወን**

10. በጋሞ ዞን ቦረዳ ወረዳ በሚገኘው ዘፈኔ ከተማ ጣቢያ 01 የእርግብ ምልክትን ያዘሉ የቅስቀሳ ሰነዶች ከጣቢያ በ200 ሜትር ርቀት ላይ ተሰተውለዋል።

**የድምጽ መስረቅ ሁነቶች**

11. በጋሞ ዞን ገራሴ ወረዳ ዱቼ ዱሻ ጣቢያ በድምጽ ቆጠራ ወቅት የጣቢያው ኃላፊዎች በጥቅም ላይ ያልዋሉ የድምጽ መስጫ ካርዶችን ሲሞሉ እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል።

**ሕገ ወጥ የድምጽ አሰጣጥ**

12. በወላይታ ዞን አረካ ከተማ ጮራ ታሬ ጣቢያ የተገኘ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢ የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ላልነበሩ ግለሰቦች ሲታደሉ እንደነበር አረጋግጧል።
13. በወላይታ ሶዶ ዞን ዱጉና ፉንጎ ወረዳ በተቋቋመው ታዲሳ 01 ጣቢያ መራጮች ድምጻቸውን ከአንድ ጊዜ በላይ ሲሰጡ እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል። በተመሳሳይ መልኩ በወላይታ ዞን አረካ ከተማ በሚገኝ ሌላ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ከአንድ ጊዜ በላይ ድምጽ የመስጠት ሁኔታ እንደነበረ ተረጋግጧል።

**ባዶ መሆናቸው ያልተረጋገጡ የድምጽ መስጫ ሳጥኖች**

14. በደራሼ ልዩ ወረዳ ጣቢያ 03 የድምጽ መስጫ ጣቢያው ኃላፊ የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን ሳያረጋግጡ።

**የምርጫ አስፈፃሚዎች ጣልቃ ገብነት**

15. በደራሼ ልዩ ወረዳ ቀበሌ 01 ጣቢያ የተመደቡ አስፈፃሚዎች በድምጽ መስጠት ሂደት ውስጥ ጣልቃ በመግባት መራጮች መምረጥ ያለባቸውን ምልክት ሲነግሯቸው እንደነበር ተረጋግጧል።

**በመራጮች መዝገብ ውስጥ ስማቸው የሌሉ መራጮች እንዲመርጡ መፍቀድ**

16. በቡርጂ ልዩ ወረዳ በሚገኝ የጣቢያ ቁጥሩ 790301059601 የሆነ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ውስጥ ቢያንስ 9 ግለሰቦች የመራጮች ካርድ ሳይዙ ስማቸው በመራጮች መዝገብ ሳይገኝ እንዲመርጡ መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል።
17. በወላይታ ዞን ጮራ ታሬ ቀበሌ ጮራ ታሬ ድምጽ መስጫ ጣቢያ 12 ስማቸው በመራጮች መዝገብ ያልሰፈሩ መራጮች እንዲመርጡ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል።
18. በወላይታ ዞን አረካ ከተማ በሚገኝ የጣቢያ ቁጥሩ 0791001054003 ID በሆነ የድምጽ መስጫ ጣቢያ ውስጥ በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው የሌሉ ግለሰቦች እንዲመርጡ መደረጉን ለማወቅ ተችሏል። እነዚህ 30 ድምጽ ቅጾች በተለየ ማሸጊያ ከተቀመጡ በኋላ ወደ ድምጽ መስጫ ሳጥኑ ውስጥ ተከተዋል።
19. በወላይታ ዞን ድጉና ጉንጎ ወረዳ ከ20 በላይ ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ያልተገኙ መራጮች እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል።

**የማይለቅ የጣት ቀለም በመራጮች ላይ አለማድረግ**

20. በ52 የተለያዩ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በአማካይ 6 መራጮች በጣታቸው ላይ በማይለቅ የጣት ቀለም ምልክት ሳይደረግባቸው እንዲመርጡ ተደርጓል።

**የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ሚስጥራዊነት መጣስ**

21. በደራሼ ልዩ ወረዳ በሚገኝ 01 ቀበሌ የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ለድምጽ መስጫነት በተከለለ ቦታ ውስጥ መራጮች ድምጽ በሚሰጡበት ሰዓት ለሙሉ ቀን ተገኝተው እንደነበር መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም ሶስት መራጮች የዚህን ድርጊት ሕገ ወጥነት ቢገልጹም አስፈፃሚዎች ወደ ተከለሉ ቦታዎች ሲገቡ ነበር። ከዚህ ድርጊት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ድርጊቶች በጋሞ ዞን ገራሴ ወረዳ በሚገኝ አንድ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ላይ ተስተውሏል።
22. በወላይታ ዞን ዳሞት ወይዴ ወረዳ በሚገኝ የድምጽ መስጫ ጣቢያ አንድ የቀበሌ ኃላፊ መራጮች ድምጽ በሚሰጡበት ወቅት የሚመርጡትን የሕዝበ ውሳኔ አማራጭ ሲመለከት እንደነበር ለማረጋገጥ ተችሏል።

**የድምጽ መስጠት ሂደት መቋረጥ**

23. በጎፋ ዞን ዛላ ወረዳ በሚገኝ የጣቢያ መለያ ቁጥሩ 0790702379803 በሆነ የድምጽ መስጫ ጣቢያ የድምጽ መስጠት ሂደቱ በአስፈፃሚዎች ከ20 ደቂቃ በላይ የተቋረጠ ሲሆን ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት በሰልፍ ላይ የነበሩ ወንድ እና ሴት መራጮችን ለመለየት ነበር።

**የድምጽ መስጫ ጣቢያን ለቀው እንዲወጡ የተጠየቁ ታዛቢዎች**

24. በወላይታ ዞን ዱጉና ፋንጎ ወረዳ ከፋከሩ ጊዶ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ቁጥር 3 የሚገኝ ታዛቢ ፍቃድ የሌላቸው ግልሰቦች ከአመሻሹ 11 ሰዓት አካባቢ ከድምጽ መስጫ ጣቢያ ለቆ እንዲወጣ እንደተጠየቀ ሪፖርት አድርጓል። ሆኖም ግን ታዛቢው ከጣቢያ እንደማይወጣ ገልጾ መታዘቡ መቀጠሉን ሪፖርት አድርጓል።

# ሐ) የድህረ-ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት

በድህረ-ሕዝበ ውሳኔ ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመከታተል ኅብረት ለምርጫ 50 ታዛቢዎችን በማሰማራት ጠቅላላ የፖለቲካ ሁኔታዎችን፣ የሕዝብ አስተያየትን እና የሲቪክ ምህዳሩን በስድስት የሪፖርት ክፍሎች በመከፋፈል ለአንድ ወር ያክል ታዝቧል። የሚከተሉት መረጃዎች የተመሰረቱት ከ50 የድህረ ምርጫ ታዛቢዎች በተሰበሰቡ 300 ሪፖርቶች ላይ ነው።

## የድህረ-ምርጫ ተቃውሞዎች

- ሁሉም 300 (100%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች በድህረ- ሕዝበ ውሳኔ ወቅት በሕዝበ ውሳኔው ሂደት ወይንም ውጤት አማካኝነት የተጠሩ የተቃውሞ ሰልፎች፣ አድማ ወይም ግጭት አለመኖራቸው እንዲሁም በመሰብሰብ እና በመንቀሳቀስ መብቶች እና ነፃነቶች ላይ የተጣሉ ክልከላዎች ወይም ገደቦች እንዳልነበሩ ገልጸዋል። በተጨማሪም በሚዲያ ባለሞያዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም አባላቶቻቸው ላይ ሲከናወን የነበሩ የጥላቻ ንግግሮች፣ ማስፈራሪያዎች እንዳልነበሩ ተገልጿል።

## በሕዝበ-ውሳኔ ውጤት ላይ የነበረው የሕዝብ አስተያየት

- 4% (11) ሪፖርቶች በሕዝበ ውሳኔው ውጤት ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ በሕዝቡ ዘንድ እንዳለ ገልጸዋል። እነዚህ ጥርጣሬዎች በስፋት የቀረበቡት በወላይታ፣ ጋሞ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ነበር።
- በሁሉም 300 (100%) ሪፖርቶች የተጋነኑ ወይም ሃሰተኛ መረጃዎች በሚዲያ ሲተላለፉ አለመታዘባቸውን ገልጸዋል።
- ሁሉም ሪፖርቶች ሕዝበ ውሳኔው በተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ዜጎች በሕዝበ ውሳኔው ውጤት ፍትሃዊ እና ተቀባይነት የሌለው እንደሆነ ሲገልጹ እንደነበር ገልጸዋል።

## በሲቪክ ምህዳር ላይ የተጣሉ ገደቦች

- በሁሉም 300 (100%) ሪፖርቶች ከህዝበ ውሳኔው ጋር በተገናኘ በጋዜጠኞች፣ ታዛቢዎች፣ ሲቪል ማህበራት ወይም ዜጎች ላይ የደረሰ እስር እንዳልነበረ ገልጸዋል።

# መ) የሕዝበ ውሳኔው ውጤት ትንተና

በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ከተካሄደው የሕዝበ ውሳኔ ምርጫ በመቀጠል ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሁሉም ጣቢያዎች ያሉ ውጤቶች የማዳመር ሥራዎችን አከናውኗል። ማዳመሩ የተከናወነው አርባምንጭ ከተማ በሚገኘው ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ነበር። የመጀመሪያ ዙር ውጤት በጥር 27 ቀን 2015 ዓ.ም የተገለጸ ሲሆን ቀጣይ ውጤቶች በተከታታይ ይፋ ሲደረጉ ነበር። ሆኖም ግን የወላይታ ዞን የሕዝበ-ውሳኔ ውጤት ቦርዱ በዞን የተካሄደውን ህዝበ ውሳኔ ሕጋዊነት ማረጋገጥ ባለመቻሉ አማካኝነት አልተገለጸም ነበር። በመቀጠልም ቦርዱ ጥርጣሬ አላባቸው በተባሉ ቦታዎች የማጣራት ሥራዎችን እንደሚሰራ እና ውጤቱንም በአፋጣኝ ለሕዝብ ይፋ እንደሚያረግ አሳውቆ ነበር።[24]

ከቦርዱ በተገኘው መረጃ መሰረት ወላይታ ዞን በሙሉ እንዲሁም በሌሎች ዞኖች እና ልዩ ወረዳዎች በሚገኙ 81 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን ሳይጨምር 1,646,425 መራጮች ድምጻቸውን አዲስ ክልል ለመመስረት በመደገፍ የሰጡ ሲሆን 78, 970 መራጮች ደግሞ በነባር ክልል ውስጥ መቆትን እንደሚፈልጉ ገልጸዋል። ቦርዱ በወላይታ ዞን ያለውን ውጤት በተመለከተ የምርጫ ህጉን በከፍተኛ ሁኔታ የጣሰ ስለነበር ውጤቱን ሰርዞታል።

በአጠቃላይ 95% መራጮች ለአዲሱ ክልል ምስረታ ድጋፋቸውን የሰጡ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ አማሮ ልዩ ወረዳ ከፍተኛውን የድጋፍ ድርሻ (100%) ይወስዳል።

24 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ National Election Board of Ethiopia. (n.d.). Retrieved from https://t.me/NationalElectionBoardNEBE/863

ከዚህ በታች የሚገኘው ሠንጠረዥ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተገለጸውን የሕዝበ-ውሳኔ ውጤት ይገልጻል።

| ተቁ | ዞን/ልዩ ወረዳ | የተመዘገቡ መራጮች | የመረጡ መራጮች | % የመራጮች ተሳትፎ | ጠቅላላ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች | በውጤት የተካተቱ ጣቢያዎች | በውጤት ያልተካተቱ ጣቢያዎች | ለጎጆ የተሰጡ ድምጾች | ለጎጆ የተሰጡ ድምጾች | % ለአዲሱ ክልል ምስረታ የተሰጡ ድምጾች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አሌ | 29,950 | 23,520 | 79% | 64 | 61 | 3 | 412 | 22,395 | 98% |
| 2 | አማሮ | 94,233 | 91,382 | 97% | 93 | 91 | 7 | 216 | 90,377 | 100% |
| 3 | ባስኬቶ | 32,639 | 29,912 | 92% | 64 | 64 | 0 | 1,133 | 27,674 | 96% |
| 4 | ቡርጂ | 36.123 | 29,943 | 83% | 39 | 27 | 3 | 765 | 28,460 | 97% |
| 5 | ደራሼ | 56,801 | 53,155 | 94% | 85 | 78 | 7 | 453 | 51,467 | 99% |
| 6 | ጋሞ | 630,340 | 602,133 | 96% | 805 | 784 | 21 | 9,682 | 583,757 | 98% |
| 7 | ጌዴኦ | 372,754 | 300,994 | 81% | 626 | 603 | 7 | 49,749 | 241,695 | 83% |
| 8 | ጎፋ | 289,307 | 264,665 | 91% | 329 | 319 | 10 | 12,306 | 243,327 | 95% |
| 9 | ኮንሶ | 111,561 | 105,292 | 94% | 135 | 131 | 4 | 1890 | 101,114 | 98% |
| 10 | ደቡብ ኦሞ | 297.948 | 266,991 | 90% | 64 | 61 | 3 | 5,364 | 256,159 | 98% |
| | **ድምር** | **1,951,656** | **1,767,987** | | **26,656** | **2578** | **81** | **78,970** | **1,646,425** | **95%** |

# ምዕራፍ 5: ማጠቃለያ እና ምክረ-ሃሳቦች

የድቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ ውሳኔ በአጠቃላይ ሰላማዊ ሆኖ አልፏል። ሆኖም ግን በመራጮች ምዝገባ እና በሕዝበ ውሳኔ ድምጽ አሰጣጥ ላይ የተስተዋሉ የተለያዩ የሕግ ጥሰቶች ተስተውለዋል። በዚህም ምክንያት የመራጮች ምዝገባ በ24 የምዝገባ ጣቢያዎች እንዲሰረዝ አድርጓል። በተጨማሪም በ81 ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እና በመላው የወላይታ ዞን ውጤቶች ተሰርዘዋል።

## ምክረ-ሃሳቦች

ኅብረት ለምርጫ የሚከተሉትን ምክረ-ሃሳቦች ከታች ለተዘረዘሩት ባለድርሻ አካላት ከቅድመ-ሕዘብ ውሳኔ፣ ሕዝበ-ውሳኔ ቀን እና ድህረ-ሕዘብ ውሳኔ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ በመመስረት ያቀርባል።

### የመራጮች ትምህርት

ሕዝበ-ውሳኔ ምርጫ ከተካሄደባቸው ስድስት ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች ስፋት አንፃር ሲታይ የመራጮች ትምህርት ላይ የተሰማሩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነበር። በዚህም ምክንያት በገጠራማ አካባቢዎች የተሰጡ የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎች አመርቂ አልነበሩም። የሲቪል ማህበራት ከገንዘብ እና የአቅም ውስነቶች ጋር በተገኛኘ ተግዳሮቶች ገጥመዋቸዋል። ለመራጮች ትምህርት የተሰጠው አጭር ጊዜም መሆን አመርቂ ላልሆነ የመራጮች ትምህርት አፈጻጸም እንደመንስኤ ይጠቀሳል። ኅብረት ለምርጫ የመራጮች ትምህርትን ለማሻሻል የሚከተሉትን ምህረ-ሃሳቦች ለመለገስ ይወዳል፤

- ሲቪል ማህበራት የመራጮች ትምህርት ፕሮጀክት እና ማናጅመንት  ጋር በተገናኙ ከፍተኛ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ሊሰሩ ይገባል።
- በዴሞክራሲ፣ አስተዳደር እና ምርጫ ላይ የሚሳተፉ የሲቪል ማህበራት ቁጥር መጨመር አስፈላጊ ነው። እነዚህ ማህበራት በተለይም በሲቪክ ተሳትፎ ማለትም በመራጮች እና የስነ-ዜጋ ትምህርት ስርጭት በመሰማራት የዜጎችን የፖለቲካ ተሳትፎ ሊያጎለብቱ ይገባል። ሲቪል ማህበራት የፈጠራ ዘዴዎችን በመጠቀም የመራጮች ትምህርትን ሊያሰራጩ ይገባል።
- ሲቪል ማህበራት የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ዘዴያቸውን በዝቅተኛ ደረጃ የተቀመጠው የመራጮች ትምህርት የጥራት ደረጃ ከማረጋገጥ አኳያ ሊፈትሹ ይገባል

- ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለመራጮች ትምህርት በቂ ጊዜን መስጠት አለበት
- በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝበ-ውሳኔ የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ለተሳተፉ ሲቪል ማህበራት የገንዘብ ድጋፍ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሰጠ ቢሆንም ይህን ድጋፍ የሚያገኙ ድርጅቶችን ቁጥር ሊያሳድግ ይገባል።
- ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በብሮድካስት ሚዲያዎች ያስተላለፋቸው ማስታወቂያዎች ይበል የሚያሰኙ ቢሆንም ቦርዱ ማስታወቂያዎችን በተለያዩ ቋንቋዎች ለማስነገር ጥረቶችን ማድረግ አለበት።
- የዓለም አቀፍ አጋሮች የሥነ-ዜጋ እና መራጮች ትምህርት በቂ የሆነ ገንዘብ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።

## ክርክሮች

- በሲቪል ማህበራት ድርጅቶች፣ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲሁም በሚዲያዎች የተዘጋጁ ክርክሮች አነስተኛ ነበሩ። በመሆኑም ሲቪል ማህበራት፣ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲሁም ሚዲያዎች ክርክሮችን በማዘጋጀት ረገድ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል።
- ሚዲያዎች መረጃን ከማሰራጨት አኳያ ቁልፍ የሚባሉ ባለድርሻ አካላት በመሆናቸው ለሲቪል ማህበራት እና ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር በምርጫዎች ወቅት ክርክሮችን ሊያዘጋጁ ይገባል።

## የሲቪክ ምህዳር

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ዕውቅና ያገኙና ኅብረት ለምርጫ ባሰማራቸው ታዛቢዎች እና በምርጫ ቦርድ ሠራተኞች እንቅስቃሴዎች ላይ ገደብ የመጣል ጥቂት ሁኔታዎች ታይተዋል። ይህም የሆነው ከአካባቢ የመንግስት ኃላፊዎች የግንዛቤ ማነስ መሆኑን ኅብረት ለምርጫ ለመረዳት ችሏል። ይህን ለመከላከል፡-

- ምርጫ ቦርድ የአካባቢ አስተዳደር ኃላፊዎችን ግንዛቤ በማሳደግ በምርጫ ሂደት ገንቢ ሚናን እንዲጫወቱ ማድረግ አለበት።

## የመራጮች ምዝገባ

- ምንም እንኳን ኅብረት ለምርጫ ከታዛቢዎቹ የደረሱት መረጃዎች በአብዛኛው ትዝብት የተደረገባቸው የምዝገባ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ሕጻናትን ለያዙ እናቶች እና የመንቀሳቀስ እክል ላለባቸው ዜጎች ተደራሽ እንደነበሩ ቢገልጹም ኅብረት ለምርጫ አመቺ እና ተደራሽ ያልነበሩ ጣቢያዎች እንዳሉ ተገንዝቧል። በመሆኑም ምርጫ ቦርድ የምዝገባ እና የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አመቺነት እና ተደራሽነት ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሥራ ማከናወን አለበት።
- የምርጫ አስፈፃሚዎች ማንነታቸውን እና መኖሪያቸውን ሳያረጋግጡ መራጮችን ሲመዘግቡ የነበረ ሲሆን አስፈፃሚዎች መራጮችን ክልክል በሆነ መልኩ በቤት ለቤት ዘመቻ ሲመዘገቡ እንደነበር ኅብረቱ ለመታዘብ ችሏል። በዚህም አማካኝነት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ24 ጣቢያዎች የተከናወኑ የመራጮች ምዝገባ ሂደቶችን ሰርዟል። ይህን ታሳቢ በማድረግ ቦርዱ የምርጫ አስፈጻሚዎችን አቅም፣ የፖለቲካ ገለልተኛነት እና ነፃነት ሊያጤን ይገባል።

## የሕዝበ-ውሳኔ ቀን

የሕዝበ ውሳኔው ቀን ሠላማዊ ሆና ያለፈ ቢሆንም ጠንካራ ግድፈቶች የተስተዋሉበት ነበር። በዕለቱ የምርጫ ቁሳቁሶች አለመሟላት፣ በተከለከሉ ቦታዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መቋቋም፣ ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች ወደምርጫ ጣቢያዎች መግባት፣ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት የቅስቀሳ ሥራዎች ማከናወን፣ የድምጽ መስጫ ሳጥኖችን በሕገ ወጥ መንገድ መሙላት፣ ሕገ-ወጥ ድምጽ አሰጣጥ፣ የድምጽ መስጫ ሳጥኖችን ባዶነት በግልጽ አለማሳየት እንዲሁም ሌሎች ጥሰቶች ተስተውለዋል። ስለሆነም፡-

- የምርጫ ቦርድ የምርጫ አስፈፃሚ ሆነው የሚቀጠሩ ሰራተኞችን ስልጠና ጥራት በማጠናከር የምርጫ ሕጉ በተጠበቀ መልኩ እንቅስቃሴዎችን እንዲያረጉ ማድረግ አለበት። ይህን በማድረግ በምርጫ ሕጉ እና መመሪያው የተደነገጉ በመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ መስጫ ቀን ወሳኝ ሁነቶች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። ቦርዱ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን ተደራሽነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አስፈላጊ እርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል።

02

# ክፍል ሁለት

# የወላይታ ዞን ድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ ትዝብት



Image: NEBE

# ምዕራፍ 6: መግቢያ

በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል በሚገኙ ስድስት ዞኖች (ኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌድዮ እና ጎፋ ዞኖች) እና አምስት ልዩ ወረዳዎች (ቡርጂ፣ ባስኬቶ፣ አሌ፣ አማሮ እና ደራሼ ልዩ ወረዳዎች) የሕዝበ ውሳኔ ምርጫ ከተካሄደ በኋላ ምርጫ ቦርድ በወላይታ ዞን በሙሉ በሚገኙ ጣቢያዎች በመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ መጠነ ሰፊ ሕገ ወጥ ተግባራት መከሰታቸውን ገልጾ በወላይታ ዞን የተደረገውን የምርጫ ውጤት በመሰረዝ ሕዝበ ውሳኔ በድጋሚ እንዲካሄድ ውሳኔ አስተላልፏል። በመቀጠልም በሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ቦርዱ ረቂቅ የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ የጊዜ ሠሌዳን በማዘጋጀት በሕዝበ ውሳኔው የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትን ለሚመለከታቸው አካላት ገልጿል። በዚህም መሰረት ድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔው በሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚከናወን ቀጠሮ ተይዞለት ነበር።[25] ከዚሁ በመከተል ከሕዝበ ውሳኔው ጋር በተገናኘ የተለያየ ሚናን ማለትም በታዛቢነት፣ በመራጮች ትምህርት ስርጭት እና በሰብዓዊ መብት ክትትል ሥራዎች ላይ ከተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር አከናውኗል። ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና ከሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ከተውጣጡ 12 ባለድርሻ አካላት ጋር ቦርዱ ምክክር አካሂዶ ነበር። [26]

በወላይታ ዞን የተካሄደው ድጋሚ ምርጫ በምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2019 አንቀጽ 10(ሀ) መሰረት " ቦርዱ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝ እና ድጋሚ ምርጫ እንዲከናወን ለመወሰን በአዋጅ ቁጥር 1162/2019 እና አዋጅ ቁጥር 1133/2019 መሰረት በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው።"

ከድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ ምርጫ ቀን ቀድሞ ሁለት በወልይታ ዞን የሚገኙ ፓርቲዎች ( የወላይታ ሕዝብ ዴሞክራሲያዎ ግንባር እና የወላይታ ብሔራዊ ንቅናቄ) ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ማስገባታቸውን አሳውቀዋል።[27] በክሳቸውም የፌደሬሽን ምክር ቤት ስድስቱን ዞኖች እና አምስቱን ልዩ ወረዳዎች በአንድ ክልል ለማደረጃት ሕዝበ ውሳኔ እንዲደረግ የወሰነውን ውሳኔ በመቃወም ፌደሬሽን ምክር ቤትን ጨምሮች ሌሎች የመንግስት አካላትን ከሰዋል።

በድጋሚ ምርጫዎች ላይ አዲስ የመራጮች መዝገብ እንደማይኖር ከሚደነግገው የምርጫ ሕግ በተቃራኒ በወላይታ በተካሄደው ድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ወቅት የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች በተመሳሳይ ቀን (ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም) ተከናውነዋል። በጠቅላላው 849,896 (418565 ሴት እና 431,331 ወንድ) መራጮች ለሕዝበ ውሳኔው ተመዝግበው ድምጻቸውን መስጠታቸውን ቦርዱ አሳውቋል።[28]

በተሰጠው ሕጋዊ ኃላፊነት መሰረት ኅብረት ለምርጫ በወላይታ ዞን በተካሄደው ድጋሚ ሕዘበ ውሳኔ ሶስቱንም የምርጫ ሂደቶች ማለትም (ቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ፣ የሕዝበ ውሳኔ ቀ እና ድህረ ሕዝበ ውሳኔ) ለመታዘብ ችሏል። በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ አባል ድርጅቶቹን አስተባብሮ በ16 ወረዳዎች እና ስድስት ከተማ መስረዳደሮች ከ ሰኔ 03 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰማሩ ስድስት የረዥም ጊዜ ታዛቢዎችን መመልመሎ፣ በማሰልጠን፣ አሰማርቷል።

የሕዝበ ውሳኔ ምርጫ ቀንን በተመለከተ ኅብረት ለምርጫ 181 ታዛቢዎች ከሰባት አባል ድርጅቶቹ በመመልመል 148 ታዛቢዎች አሰማርቷል (28 ተንቀሳቃሽ እና 120 ተቀማጭ ታዛቢዎችን)። ከነዚህ ውሳጥ 36 በመቶ የሚሆኑት ታዛቢዎች ሴቶች ናቸው። ይህ ሪፖርት ከ117 ታዛቢዎች (32 % ሴት እና 68% ወንድ) በተሰበሰቡ ሪፖርቶች ላይ የተመሰረተ ነው። በተጨማሪም እነዚህ ከታዛቢዎች የሚመጡ ሪፖርቶች (አሳሳቢ ሁኔቶችን ጨምሮ) የሚሰበሰቡበት፣ የሚጠናቀሩበት፣ እና የሚረጋገጡበት የመረጃ ማዕከል አዲስ አበባ በሚገኘው ጽህፈት ቤቱ አቋቁሞ ነበር።

25 "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል በሚገኘው የዎላይታ ዞን ላይ የሚያካሄደው የድጋሚ ሕዝበ ውሣኔ የትግበራ አፈጻጸም ዝርዝር ዕቅድ ማሳያ ረቂቅ የጊዜ ሠሌዳ." National Electoral Board of Ethiopia. Accessed on July 1, 2023. https://www.nebe.org.et/am/node/216.

26 "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በወላይታ ዞን የሚካሄደውን የድጋሚ ሕዝበ ውሣኔን ምርጫ በተመለከተ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጋር ምክክር አካሄደ." National Electoral Board of Ethiopia. Accessed on July 1, 2023. https://www.nebe.org.et/am/node/22.

27 Ethiopia Insider. "ሁለት የወላይታ ፖለቲካ ፓርቲዎች በፌዴሬሽን ምክር ቤት ላይ ክስ መሰረቱ." (Accessed on July 26, 2023). https://ethiopiainsider.com/2023/11133/.

28 National Electoral Board of Ethiopia. "Wolaita Zone Referendum." (Accessed on July 26, 2023). https://www.nebe.org.et/sites/default/files/wolaiya_Zone_Referendum.jpg.

# ምዕራፍ 7: የቅድመ -ድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት ግኝቶች

ይህ ሪፖርት በወላይታ ዞን ውስጥ በቅድመ ሕዝበ-ውሳኔ ወቅት ስለነበረው አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ምልከታን ይዳስሳል። የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) እያንዳንዱን ምርጫ እንደ ሂደት የሚመለከት ሲሆን ከድምጽ መስጫ ቀን በፊት ያለውን አጠቃላይ ሁኔታን ከሰኔ 10 እስከ ሰኔ 19 ቀን 2015 ዓ.ም. ድረስ በ16ቱ ወረዳዎች በመገኘት የሚታዘቡ ስድስት የረዥም ጊዜ ታዛቢዎችን መልምሎ፣ በማሰልጠን፣ አሰማርቷል እና ስድስት የረጅም ጊዜ ታዛቢዎችን አሰማርቷል። የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደትን ፣ የድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ ቅስቀሳዎች እና የሲቪክ ምህዳት እንዲሁም የደህንነት ሁኔታዎችን ታዝበዋል። የሚከተሉት ክፍሎች በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያለውን የትዝብት ግኝቶችን ያካትታሉ፣

## የመራጮች ትምህርት

በወላይታ ዞን ድጋሚ ሕዝበ ሕዝበ-ውሳኔ ከመከናወኑ አስቀድሞ ሰባት የሲቪክ ማህበራት የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ግንቦት 25 ቀን 2015 ዓ.ም ከቦርዱ ጋር ተመካክረዋል። የሲቪክ ማህበራቱ በወላይታ ዞን በሚገኙ አካባቢዎች በሙሉ የመራጮች ትምህርትን ለመስጠት እንዲያስችላቸው በዞኑ የሚገኙትን 16 ወረዳዎች እና ስድስት የከተማ አስተዳደሮች በመካከላቸው ተከፋፍለው ነበር።[29]

### ዝርዝር ግኝቶች

***የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎች መኖር***

- ሁሉም፣ 12(100%)፣ ከታዛቢዎች የተላኩ ሪፖርቶች ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው አካባቢዎች የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎችን እንደነበሩ አመላክተዋል።
- 3(25%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች ምርጫ ቦርድ በየእለቱ የመራጮች ትምህርት በአካባቢ ራዲዮ ይሰጥ እንደነበር ገልጸዋል። 1 (8%) የታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያመለከተው የመራጮች ትምህርት በየሳምንቱ ይሰጥ እንደነበር ሲሆን 8(67%) ታዛቢዎች አንድ ጊዜ ብቻ እንደተደረገ ሪፖርት አድርገዋል።
- ሁሉም፣ 12(100%)፣ ከታዛቢዎች የተላኩ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት የድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔውን ቀን፣ የሕዝበ ውሳኔውን አማራጮች በሕዝበ ውሳኔው በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ የመታወቂያ ሰነዶች እንዲሁም የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ በተመሳሳይ ቀን እንደሚከናወኑ ሲሰጡ በነበሩ የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተካተው እንደነበር ገልጸዋል።

***የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ***

የመራጮች ትምህርት ለመስጠት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማለትም የገጽ ለገጽ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን፣ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች (Billboards) እና የህትመት ሚዲያዎችን ፣ የመንገድ ትርኢቶችን፣ የአካባቢ ሚዲያዎችን (ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን) ፣ማህበራዊ ሚዲያ; እንዲሁም የተለያዩ ዘዴዎች በማጣመር ሲከናወኑ ነበር።

- 11(92%) ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት ከአንድ በላይ በሆነ መንገድ መካሄዱን አመልክተዋል። 1(8%) ሪፖርት እንደሚያሳየው የመራጮች ትምህርት በቢልቦርድ እና በሕትመት አማካይነት ብቻ መከናወኑን ያሳያል።

***የመራጮች ትምህርት ተደራሽነት***

- 8(67%) ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት የመራጮች ትምህርት እንቅስቃሴዎች በከተማም ሆነ በገጠር ለሚኖሩ መራጮች በቀላሉ ተደራሽ ነበሩ። ሆኖም ግን 3(25%) ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት የከተማ አካባቢዎች በቀላሉ ለመራጮች ትምህርት ተደራሽነት እንደነበራቸው እንዲሁም በ1(8%) ሪፖርት መሰረት ደግሞ የገጠር አካባቢዎች ብቻ በቀላሉ ተደራሽ እንደነበር ገልጸዋል።
- 10(83%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት ሁለቱንም ጾታዎች እና አካል ጉዳተኞችያካተተ እንደነበር አሳይተዋል።
- 10(83%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት በመስጠት ላይ የሴቶች እና የአካል ጉዳተኞች እኩል ተሳትፎ እንደነበረ ገልጸዋል።

29 https://nebe.org.et/am/node/868

**ያጋጠሙ ተግዳሮቶች**

- 6 (50%) ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት የመራጮች ትምህርት ሰጪዎች የገጠማቸው ዋነኛው ተግዳሮት ትምህርቱን ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለሌሎች የተገለሉ ቡድኖች ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ሲሆን በ4 (33%) ከታዛቢዎ የደረሱ ሪፖርቶች የቋንቋ እና የባህል እንቅፋቶችን እንደፈጠሩ እንዲሁም 2 (17%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች የገንዘብ እጥረትን እንደ ተግዳሮት ጠቅሰዋል።
- የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የሚሰጠውን የመራጮች ትምህርት ጥራት እና ውጤታማነት በሚከተሉት መለኪያዎች ላይ በመመርኮዝ ገምግመዋል።
  - ተደራሽነት፡ የመራጮች ትምህርት ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች የተዳረሰበትን መጠን
  - ትክክለኝነት ፡ በመራጭ ትምህርት ቁሳቁሶች ውስጥ የተሰጠው መረጃ ትክክለኛነት;
  - ግልጽነት፡ በመራጮች ትምህርት ቁሳቁሶች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው የቋንቋ እና የመልዕክት ግልጽነት;
  - ተሳትፎ፡ በመራጮት ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ያለው የሕብረተሰቡ ተሳትፎ።
- በዚህ መሰረት ታዛቢዎች የመራጮችን ትምህርት ጥራት እንዲገመግሙ ተጠይቀዋል።
  - 7 (58%) ፍትሃዊ፣
  - 2 (17%) ደካማ
  - 2 (17%) ጥሩ እና
  - 1(8%) በጣም ጥሩ በማለት ገምግመዋል።
- ታዛቢዎች በመራጮች ትምህርት በጥቅም ላይ የዋለውን መልእክት ውጤታማነት እንዲገመግሙ ተጠይቀው ሁሉም 12 (100%) ታዛቢዎች በመራጮች ትምህርት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለውን መልእክት በመጠኑ ውጤታማ በማለት ገምግመውታል።

# የቅስቀሳ ዘመቻዎች

በማንኛውም የምርጫ ወይም ህዝበ ውሳኔ ሂደት ቁልፍ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የቅስቀሳ ዘመቻ ነው፣ ይህም መራጮች በድምጽ ስለሚሰጧቸው የተለያዩ አማራጮች ግንዛቤን ይፈጥራል። በመሆኑም ከህዝበ ውሳኔው በፊት ተደራሽ እና እኩል የሆነ የዘመቻ አካባቢ ለአጠቃላይ የምርጫ ሂደቱ አስፈላጊ ነው። የ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የቅስቀሳ ዘመቻዎችን እንዲከታተሉ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። በወላይታ ዞን በተካሄደው ድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ የቅስቀሳዎች ተደራሽነት እና ለሕዝበ ውሳኔው አማራጮች የተሰጣቸውን ዕድል ተመልክተዋል።

የህዝበ ውሳኔ ድጋሚ ምርጫ ምርጫዎቹን የሚወክሉ ሁለት ምልክቶች የነበሩት ሲሆን "ነጭ ርግብ" ምልክት ለአዲስ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መፈጠር የቆመ ሲሆን "የጎጆ" ምልክት ደግሞ በነባር ስር ያሉትን ስድስቱ ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች በነበሩበት ክልል ውስጥ እንዲቀጥሉ የሚደግፍ ነው። በዚህም መሰረት

- ሁሉም 12(100%) የታዛቢ ሪፖርቶች የቅስቀሳ እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ ገልጸዋል
- 6(50%) ሪፖርቶች የተካሄዱ የቅስቀሳ ዘመቻዎች ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ተደራሽ እንዳልነበሩ ያስረዳሉ። ይህ ሊሆን የቻለው የቅስቀሳ ሥራዎችን ለማሰራጨት በጥቅም ላይ የዋሉት የአሰጣጥ ዘዴዎች የመንገድ ላይ ትርዒቶች እና የሕትመት ዘዴዎችን በመጠቀም የተሰቱ በመሆናቸው ነው። በተጨማሪም የቅስቀሳ ዘመቻዎች የተከናወኑት በብዛት በከተማ አካባቢዎች ነበር። ከዚህም ባላይ ዘመቻዎቹ የሕዝበ ውሳኔ አማራጮቹን በሚገባ አልዳሰሱም ነበር።
- 10 (83%) የታዛቢ ሪፖርቶች ከሕዝበ ውሳኔ ጋር በተገናኘ በተደረጉ የቅስቀሳ ዘመቻዎች ምንም አይነት ረብሻዎች፣ ጠብ የሚጭሩ ንግግሮች፣ የተዛቡ መረጃዎች፣ የጥላቻ ንግግሮች እንዳልነበሩ ሲጠቁሙ 2(17%) ሪፖርቶች ደግሞ እነዚህ ሁኔታዎች እንደተከሰቱ ገልጸዋል። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ያቀረቧቸው ሪፖርቶች በማህበራዊ ሚዲያ በተለይም በፌስ ቡክ የተስተዋሉ ሁኔታዎጵ መኖራቸውን ማለትም አንዳንድ የማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎች (activists) በዞን እና በወረዳ አመራሮች ላይ ጠብ የሚያነሳሱ ንግግሮችን ሲያደርጉ እንደነበር ገልጸዋል። እንደ ረዥም ጊዜ ታዛቢዎች ሪፖርት ከሆነ አንዳንድ የማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎች ለሕዝበ ውሳኔው የቀረቡት አማራጮች የወላይታን ህዝብ ፍላጎት በፍጹም እንደማይወክሉ ገልጸዋል።
- 8(67%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች የተከናወኑ የቅስቀሳ ዘመቻዎች የሕዝበ ውሳኔውን አማራጮች በእኩልነት ለሕዝብ እንዳላስረዱ ገልጸዋል። እነዚህ ቅስቀሳዎች ለአንዱ አማራጭ (ለነጭ እርገብ አማራጭ) ያደሉ ሲሆን የአዲሱን ክልል መመስረት የሚደግፉ ነበሩ።
- የቅስቀሳ ዘመቻዎች ላይ ገደብ የጣሉ ድርጊቶችን መኖራቸውን የጠቆሙ ሪፖርቶች ለኅብረት ለምርጫ አልደረሱም።

## ክርክሮች

ሌላኛው የማንኛውም የምርጫ ወይም ህዝበ ውሳኔ ወሳኝ ሂደት የምርጫ ወይም የህዝበ ውሳኔ አማራጮችን በሙግት በማቅረብ ለማህበረሰብ የሚያስረዱ ክርክሮች ናቸው። ማንኛውም ክርክር የሚከተሉትን መርሆዎች ማካተት አለበት፡- ሁሉም ተከራካሪዎች ሃሳባቸውን የሚገልጹበት ፍትሃዊ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል፣ የክርክር አወያዮች ገለልተኛ መሆን አለባቸው፣ ክርክሮች የሚከናወኑባቸው ሕጎች እና መመሪያዎች ለሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ግልጽ እና አተገባበራቸው ደግሞ ተመሳሳይ መሆን አለባቸው የሚሉ ናቸው። በዚህም መሰረት፡-

- 10(83%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች በቦርዱ ወይም በሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የተዘጋጁ ክርክሮች እንዳልነበሩ ገልጸዋል
- ሆኖም ግን 2(17%) ሪፖርቶች በወላይታ ወጋታ ኤፍ ኤም 96.6 ራዲዮ ጣቢያ የተላለፈ ክርክር እንደነበር አስረድተዋል፣ በዚህ ክርክር ላይ የተላኩ የታዛቢዎች ግኝቶች የሚከተሉትን ያስረዳሉ፥
  - ሁለቱን የሕዝበ ውሳኔ አማራጮች የወከሉ ተከራካሪዎች በክርክሩ በዕኩል መጠን ዕድል እንዳልተሰጣቸው
  - ክርክሩን በአወያይነት ሲመሩ የነበሩ አወያይ ገለልተኛ አልነበሩም

# ምዕራፍ 8: የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ቀን የትዝብት ግኝቶች

ኅብረት ለምርጫ በወላይታ ዞን በድጋሚ የተካሄደውን ሕዝበ ውሳኔ የመታዘቡ ዋና ግብ በሂደቱ ላይ ሲስተማቲክ (systematic) እና ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብ ግልፅነት እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የበኩሉን አስተዋፅዖ ማበርከት ነው። ከዚህ አንጻር ኅብረቱ ያሰማራቸው ተቀማጭ ታዛቢዎች በየተመደቡበት የምርጫ ጣቢያ ከማለዳው 11፡30 በመገኘት ሁሉንም የድምፅ አሰጣጥ ሂደቶች ጊዜያዊ የሕዝበ ውሳኔ ውጤት መለጠፍን ጨምሮ ሂደቱን መታዘብ እና ሪፖርርት ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎች በበኩላቸው በበርካታ የምርጫ ጣቢያዎች በመዘዋወር የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን መታዘብ እንዲሁም አሳሳቢ ሁነቶች ሲከሰቱ የኅብረት ለምርጫ ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ

1. የምርጫ አስፈፃሚዎች ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ የምርጫ ጣቢያዎች ለድምጽ መስጠት ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከመክፈቻ ሰአቱ በፊት ወደ ምርጫ ጣቢያ ይደርሳሉ። የኅብረቱ ታዛቢዎች ከጠዋቱ 11፡30 ላይ በየተመደቡባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ሲደርሱ 97በመቶ በሚሆኑት ጣቢያዎች በአማካኝ 5 የምርጫ አስፈፃሚዎችን መኖራቸውን ታዝበዋል።
2. ኅብረት ለምርጫ በታዘበባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም ኅብረቱ ያሰማራቸውታዛቢዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች እንዲገቡ እና እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸው ነበር።

## የምርጫ ጣቢያዎች አከፋፈት

3. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች ከማለዳው 12 ሰአት ጀምሮ ክፍት መሆን አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ የተጀመረው ከማለዳው 12 ሰአት እስከ 1፡00 ሰአት ድረስ ነው።
4. የምርጫ ህጉ እንደ ወታደራዊ ካምፖች፣ የግል መኖሪያ ቤቶች፣ ፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሀይማኖት ተቋማት ቅጥር ውስጥ ፣ በጤና ተቋማት፣ በመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽህፈት ቤቶች ባሉ ቦታዎች የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ይከለክላል። በዚህም መሰረት ኅብረቱ ከታዘባቸው መካከል 98 በመቶ የሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ህጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች መቋቋማቸውን ነገር ግን በኦፋ ወረዳ ገሱባ -1 ቀበሌ 07 አንድ የምርጫ ጣቢያ የምርጫ ህጉ ከደነገገው በተቃራኒ በጤና ጣቢያ ውስጥ መቋቋሙን መታዘብ ተችሏል።
5. የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ የምርጫ ህጉ በድምጽ መስጫ ቀን ከምርጫ ጣቢያዎች በ200 ሜትር ርቀት ውስጥ ምንም አይነት የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግን በግልፅ ይከለክላል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በድምጽ መስጫ ቀን ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ውስጥ ምንም አይነት ቅስቀሳ (100በመቶ) አለመደረጉን የኅብረቱ የታዛቢዎች ሪፖርት ያመለክታል።

# የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት

6. ኅብረቱ የታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙበትን ቦታ በተመለከተ 23 በመቶው በከተሞች ፤ 8 በመቶው በከፊል ከተሞች እና ቀሪው 69 በመቶው ደግሞ በገጠር አካባቢ የተቋቋሙ መሆናቸውን ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።
7. ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሃይ የሚያስጠልሉ ዳሶች መኖር በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት አስፈላጊ ክፍል ነው። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ከተሰማሩባቸው 33 በመቶዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች ነበሯቸው።
8. የምርጫ ጣቢያዎችን በተገቢው መንገድ ተቋቁመዋል ለማለት የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች መሟላት አለባቸው። ኅብረት ለምርጫ ያሰማራቸውን ታዛቢዎች አስፈላጊ የሆኑ እንደ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ ሕጋዊ የቦርዱ ማህተም፣ የውጤት ማመሳከሪያ ቅጽ፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን ፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን ማሸጊያ እንዲሁም የቅሬታ መቀበያ ቅጾች ያሉ የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች መሟላታቸውን እንዲያረጋግጡ ተጠይቀው ነበር። በዚህም መሰረት የቅሬታ መቀበያ ቅጾች ካልተሟሉባቸው 2 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች በስተቀር በሁሉም ጣቢያዎች የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው ነበር።
9. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ከመጀመራቸው አስቀድሞ የመራጮች መዝገብ እና የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች በሁሉም የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ከመጀመራቸው በፊት የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን አሳይተው ነበር።
10. የምርጫ ሕጉ በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ቢያንስ ሶስት አስፈፃሚዎች መገኘት እንዳለባቸው ያስቀምጣል። ነገርግን በወላይታ ዞን በተደረገው የድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ጣቢያ መገኘት ያለባቸው ዝቅተኛ የአስፈፃሚዎች ቁጥር ከሶስት ወደ አምስት ከፍ ተደርጓል። ምንም እንኳን ቦርዱ ይህንን መመሪያ ቢያስተላልፍም በሶዶ ዙሪያ በሚገኙ ሶስት የምርጫ ጣቢያዎች ከቦርዱ መመሪያ ውጭ ሶስት የምርጫ አስፈፃሚዎች ብቻ ተገኝተው ነበር። እነዚህ የምርጫ ጣቢያዎችም ሁምቦ ላሬና የምርጫ ጣቢያ ሁምቦ ላሬና 3 ፣ የቁራ ምርጫ ጣቢያ - 1 እና ዌሺ ጋሌ የምርጫ ጣቢያ ዌሺ ጋሌ 'ለ' ናቸው።
11. የምርጫ ሕጉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በምርጫ ጣቢያዎች ያቋቁማል። በዚህም መሰረት ኅብረቱ ከታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል በ20 በመቶዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የተቋቋሙ ቢሆንም ፤ በ80 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አልተቋቋሙም።
12. ኅብረቱ ከታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 8 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በኅብረት ለምርጫ ከተሰማሩ ታዛቢዎች ውጪ ሌሎች ታዛቢዎች የተገኙ ሲሆን 92 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በኅብረት ለምርጫ የተሰማሩ ታዛቢዎች ብቻ ተገኝተው ነበር።

# በሕዝበ ውሳኔው ሂደት የሴቶች ተሳትፎን በተመለከተ

13. ኅብረት ለምርጫ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በአማካኝ 5 የምርጫ አስፈፃሚዎች የተገኙ ሲሆን ከእነዚህ መካከል በአማካይ 2ቱ ሴቶች ነበሩ።
14. ኅብረቱ ታዛቢዎቹን ካሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 31 በመቶ የሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ኃላፊዎች ሴቶች ነበሩ። በተለየ ሁኔታ በሶዶ ከተማ ቁራ ቀበሌ የምርጫ ጣቢያ 09 ሁሉም የምርጫ አስፈጻሚዎች ሴቶች ሆነው ተስተውለዋል።
15. ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከነበሩ የጸጥታ ሃይሎች መካከል 30 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ነበሩ።

# ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ ለሚያጠቡ እናቶች እና እርጉዝ ሴቶች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት

16. ከምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት አንጻር ሌላው ወሳኝ ጉዳይ እንደ አረጋውያን፣ ህጻናትን የያዙ እና አካል ጉዳተኞችን እና መሰል የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት ነው። ከዚህ አኳያ ኅብረቱ ከታዘበባቸው መካከል 90 በመቶ የሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከላይ ለተጠቀሱት መራጮች ተደራሽ ሲሆኑ 10 በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች ግን ተደራሽ አልነበሩም።
17. ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኅብረቱ ታዛቢዎች የተመለከቱት ሌላው ጉዳይ የምርጫ ጣቢያዎች ለሁለቱም ጾታዎች (ወንድ እና ሴት) ያላቸውን ተደራሽነት የሚመለከት ሲሆን ኅብረቱ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 99በመቶ የሚሆኑት ለወንድ እና ለሴት መራጮች ተደራሽ እንደነበሩ ያመለክታል።

# የመራጮች ምዝገባና ድምጽ አሰጣጥ ሂደት

18. ሁሉም የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች በመራጮች ምዝገባ እና በድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ወቅት ከጣቢያው ለቀው እንዲወጡ አልተጠየቁም።
19. የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው 99በመቶ በሚሆኑት ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች፣ ነፍሰጡር ሴቶች እና ህጻናት ልጆች ለያዙ ወላጆች ቅድሚያ እንዲሰጥ አድርገዋል።
20. ትዝብት ከተደረገባቸው 92 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች አካል ጉዳተኞች በመረጡት የግል ረዳት እገዛ እንዲያገኙ ተፈቅዶላቸዋል። በሌላ በኩል 8 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ምንም የተለየ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው መራጮች እንዳልታዘቡ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።
21. የምርጫ ህጉ መራጮች ለመመዝገብ እና ድምጽ ለመስጠት የነዋሪነት እና የማንነት ማረጋገጫ ማሳየት እንዳለባቸው ይደነግጋል። በመሆኑም ነዋሪነታቸውን እና ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ለማቅረብ የማይችሉ መራጮች በምዝገባና በድምጽ መስጠት ሂደት ውስጥ መሳተፍ አይችሉም። በዚህም መሰረት ኅብረቱ ታዛቢዎቹን ካሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል:-
    - 59 በመቶ በሚሆኑት የማንነት እና የመኖሪያ ቦታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው ምክንያት ለመራጭነት እንዳይመዘገቡ የተከለከሉ መራጮች አልነበሩም።
    - 35 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 የሚሆኑ መራጮች ማንነታቸውን እና መኖሪያ አድራሻቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው እንዲመዘገቡ እና ድምጽ እንዲሰጡ አልተፈቀደላቸውም።
    - ታዛቢዎቹ ከጎበኟቸው 6 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከ11 አስከ 20 የሚሆኑ መራጮች የማንነት እና የነዋሪነት ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻላቸው እንዲመዘገቡ እና ድምጽ እንዲሰጡ አልተፈቀደላቸውም።
22. የምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች እየተከናወኑ ባለበት ወቅት ከሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም አንስቶ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የተሰጡ የቀበሌ መታወቂያ ካርዶችን ይዘው የሚመጡ ዜጎችን እንዳይመዘግቡ እና እንዳያስመርጡ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ አስፈፃሚዎቹ መመሪያ ሰጥቶ ነበር። በተጨማሪም ቦርዱ ምንም እንኳን የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ቢኖራቸውም እድሜያቸው ለመምረጥ ያልደረሱ የሚመስሉ መራጮች እንዳይመዘግቡም ከለከሏል።
    - 13 በመቶ በሚሆኑት እና የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 የሚደርሱ መራጮች የማንነት እና የመኖሪያ ማረጋገጫ ሰነዶችን ቢያቀርቡም እንዲመዘገቡና እንዲመርጡ አልተፈቀደላቸውም።
    - 1 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከ11 እስከ 20 የሚሆኑ መራጮች የማንነት እና የመኖሪያ ቦታ ማረጋገጫ ቢያቀርቡም መመዝገብ እና መምረጥ አልቻሉም።
    - በተመሳሳይ መልኩ 1 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከ20 በላይ መራጮች የማንነት እና የመኖሪያ ቦታ ማረጋገጫ ቢያቀርቡም መመዝገብ እና መምረጥ አልቻሉም።
23. የምርጫ ህጉ መራጮች ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት በጣታቸው ላይ የማይጠፋ ቀለም እንዲቀባ ያዛል። በዚህ መሰረት ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች 98 በመቶ በሚሆኑት የማይጠፋ ቀለም በአግባቡ በመራጮች ጣት ላይ የተደረገ ሲሆን ፤ 2 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች ከ1 እስከ 10 በሚሆኑ መራጮች ጣት ላይ የማይጠፋ ቀለም አልተቀባም።
24. የምርጫ ቦርድ በዚህ የድጋሚ ሕዝበውሳኔ የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ መስጠት በተመሳሳይ ቀን እንዲካሄድ በማድረጉ በሁሉም የህብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በታዘቡባቸው ጣቢያዎች ማንም መራጭ ሳይመዘግብ እንዲመርጥ አልተፈቀደለትም።
25. የምርጫ ህጉ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች ሁሉንም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት ማህተም እንዲያደርጉባቸው ይጠይቃል። በአንድ አጋጣሚ ብቻ (በሶዶ ከተማ ቶሜ ገራራ ምርጫ ጣቢያ 4) አንድ መራጭ ማህተም ያልተደረገበት የድምጽ መስጫ ወረቀት ተጠቅሞ ድምጽ የሰጠበት ሁኔታ ተስተውሏል። ነገርግን የምርጫ አስፈጻሚዎች ከህጉ በተጻረረ መልኩ በድምፅ ቆጠራ ወቅት በወረቀቱ ላይ ማህተም በማድረግ እና እንዲረጋገጥ በማድረግ እንዲቆጠር አድርገዋል።
26. የድምጽ መስጠት ሂደት ምስጢራዊነት ትዝብት በተደረገባቸው 98 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ቀኑን ሙሉ ተጠብቆ ነበረ።
27. ህብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹን በማሰማራት በታዘባቸው ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የድምጽ መስጫ ሳጥኖች ግልጽ በሆነ ቦታ ላይ ተቀምጠው ይታዩ ነበር።
28. በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች መገኘትን በተመለከተ 1 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጠት ሂደቱ እየተከናወነ በነበረበት ጊዜ ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተገኝተው ነበር። እነዚህ ጥሰቶች በዚህ ሪፖርት የአሳሳቢ ሁነት ክፍል ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል።

29. በእለቱ ትዝብት ከተደረገባቸው ጣቢያዎች መካከል 1 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የምዝገባ እና ድምጽ የመስጠት ሂደቱ ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦ ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያት የነበረው የምርጫ ቦርድ ካለፉት ስድስት ወራት ወደዚህ አዲስ መታወቂያ ካርድ የወሰዱ ነዋሪዎች እንዳይመዘገቡ ለምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ባስተላለፈው መመሪያ ምክንያት ነው፡፡
30. በአንድ የምርጫ ጣቢያ (1 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች) የማስፈራራት እና የማዋከብ ድርጊቶች እንደነበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል፡፡ እነዚህ ጥሰቶች በዚህ ሪፖርት የአሳሳቢ ሁነት ክፍል ውስጥ በዝርዝር ተገልጸዋል፡፡
31. ኅብረት ለምርጫ በሕዝበ ውሳኔው የድምጽ አሰጣጥ ሂደት ወቅት ተሳታፊ በነበሩ ሴት መራጮች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች እና ታዛቢዎች ላይ የማስፈራራት እና የማዋከብ ተግባራት ስለመፈፀማቸው ምንም አይነት ሪፖርት አልደረሰውም፡፡
32. 82 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጠት በተደረገባቸው ሰዓታት በሙሉ የጸጥታ አካላት ከምርጫ ጣቢያው ውጭ ተገኝተው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ 9 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ውጭ የጸጥታ አካላት ለተወሰኑ ሰዓታት የተገኙ ሲሆን በቀሪዎቹ 9 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ውጭ ላይ ግን ምንም አይነት የጸጥታ አካላት አልነበሩም፡፡
33. ምርጫ ቦርድ በሚያዘው መሰረት የሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ህጋዊ የመዝጊያ ሰዓት ከምሽቱ 12 ሰዓት የነበረ ቢሆንም በእለቱ ቦርዱ የድምጽ መስጠት ሂደቱን እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ድረስ እንዲራዘም አድርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 7.7 በመቶ የሚሆኑት ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት በፊት፣ 71.8 በመቶ የሚሆኑት ከምሽቱ 12፡00 እስከ 1፡00 ሰአት ባለው ጊዜ የተዘጉ ሲሆን ቀሪዎቹ 20.5 በመቶ የሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች ከምሽቱ 1፡00 በኋላ ተዘግተዋል፡፡
34. ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች 39 በመቶ በሚሆኑት ምርጫ ቦርድ ባስቀመጠው መዝጊያ ሰዓት (ከምሽቱ 1፡00 ሰአት) ድረስ ድምጽ ለመስጠት ሰልፍ ላይ የነበሩ መራጮች ድምጽ እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው ሲሆን በቀሪዎቹ 61 በመቶ በሚሆኑት ጣቢያዎች ላይ በመዝጊያ ሰአት ላይ ምንም አይነት የድምጽ ሰጪዎች ሰልፍ አልነበሩም፡፡

# የድምፅ ቆጠራ

35. ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸው ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት ታዛቢዎቹ ከምርጫ ጣቢያው ለቀው እንዲወጡ አልተጠየቁም፡፡
36. የምርጫ ህጉ የድምጽ ቆጠራ በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸው ሁሉም ጣቢያዎች ላይ ቆጠራ የተካሄደው በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ነበር፡፡
37. የኅብረቱ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የቆጠራው ሂደት የተቋረጠበት ሁኔታ አልተስተዋለም፡፡
38. 1 በመቶ በሚሆኑት ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በቆጠራው ሂደት ወቅት ጣልቃ ገብነት፣ ወከባ እና/ወይም ማስፈራራት እንደነበር ሪፖርት ተደርጓል፡፡ ይህም በአሳሳቢ ኹነት ክፍል በዝርዝር ተካቷል፡፡
39. ትዝብት በተደረገባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በድምፅ ቆጠራው ወቅት ሁሉንም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በግልፅ አሳይቷል፡፡
40. የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የጣቢያዎቹ ኃላፊዎች የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ዋጋ ያላቸው መሆንና አለመሆናቸውን ለመወሰን ወጥነት ያላቸውን መመዘኛዎችን በቋሚነት ተጠቅመዋል፡፡
41. 96 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች የማመሳከሪያ እና የውጤት ቅጽ ቅጂዎች ከምርጫ ጣቢያው ውጪ ተለጥፈው ነበር፡፡ በአንፃሩ የኅብረቱ ታዛቢዎች በታዘቡባቸው 4 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች የማመሳከሪያ እና የውጤት ቅጽ ቅጂዎች ከምርጫ ጣቢያው ውጪ አለመለጠፋቸውን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን ፤እነዚህ ምርጫ ጣቢያዎችም ጊዶ ምርጫ ጣቢያ 02፣ ጣዲሳ ምርጫ ጣቢያ 05፣ ኮዶ ምርጫ ጣቢያ ኮዶ፣ ጊዶ ምርጫ ጣቢያ 01፣ ዋርቢራ ሱቄ ምርጫ ጣቢያ ሱኬ 'ለ'2 ናቸው፡፡

# አሳሳቢ ኹነቶች

አሳሳቢ ኹነቶች በጠቅላላ የሕዝበ ውሳኔ ሂደቶች እንዲሁም ውጤት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ከምርጫ ሕጉ ያፈነገጡ ከባድ የአሰራር ግድፈቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ኅብረት ለምርጫ ሁሉም ታዛቢዎቹ እነዚህ አሳሳቢ ሁነቶች በሚከሰቱበት ወቅት በአፋጣኝ ወደ መረጃ ማዕከሉ ሪፖርት እንዲያደርጉ መመሪያ አስተላልፈዋል፡፡ በዚህም መሰረት የኅብረት ለምርጫ የመረጃ ማዕከል ባለሞያዎች የአሳሳቢ ሁነት ሪፖርት በሚደርሳቸው ወቅትም በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ማጣራት እና ምርመራ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በታች በዝርዝር በቀረበው መሰረት ኅብረት ለምርጫ በድምሩ ስምንት (8) የየአሳሳቢ ኹነት ሪፖርቶችን ከተቀማጭ እና ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎቹ ተቀብሏል፡-

## 1. ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት

ቦዲቲ፣ ጨጫ ለ ምርጫ ጣብያ አንድ ወጣት በቀበሌ ሰራተኞች እና በምርጫ አስፈጻሚዎች መካከል ተፈጥሮ የየነበረ አለመግባባትን ተጠቅሞ ረብሻ ለመፍጠር ሞክሮ ነበር። በአካባቢው ምንም የጸጥታ አካላት ካለመኖራቸውም ባላይ፣ ተደውሎላቸው ሲመጡም ለአስፈፃሚዎች ጥሩ ምላሽ እንዳልሰጡ የኅብረቱ ታዛቢ ሪፖርት ተደርጓል። በዚሁ የምርጫ ጣቢያ የቀበሌ ሰራተኛ መሆኗ የተገለፀ አንዲት ሴት መታወቂያ ያልያዙ 3 ወጣት ወንዶችን አስከትላ ወደ የምርጫ ጣብያ ውስጥ በመግባት እራሷን እና ሶስቱን ወጣት ወንዶች መምረጥ አለብን በማለት ጫና ለመፍጠር ሞክራ ነበር።

## 2. በቆጠራ ሂደት ወቅት ያጋጠሙ የማስፈራራት እና የማዋከብ ተግባራት

ቦዲቲ፣ ጨጫ ለ ምርጫ ጣብያ አንድ ያልተፈቀደለት (በኋላ በጣቢያው በተሰማራ ታዛቢ በተደረገ ማጣራት የማዘጋጃ ቤት ሰራተኛ ነው የተባለ) ግለሰብ በተደጋጋሚ ምርጫ ጣብያ ውስጥ በመግባት ያልተገባ ጫና ለመፍጠር ሲሞክር ነበር። ይህ ግለሰብ ወደጣቢያው በመግባት የኅብረቱን ታዛቢ 'ሌላ ቦታ አልሰማህም እንዴ? ውጤቱ እኮ ይታወቃል፣ እናንተ መራጮች እየመለሳችሁ ነው። ብዙ መራጭ ተመልሷል፣ አስመርጧቸው' በማለት ጫና ለመፍጠር ሞክሯል። የምርጫ አስፈፃሚዎቹም ምንም አይነት ግለሰቡን ከጣቢያ የማስወጣት ሙከራ አላደረጉም።

## 3. እንዳይመዘገቡና ድምጽ እንዳይሰጡ የተከለከሉ መራጮች

ዳሞት ጋሌ ወረዳ፣ ቡጌ ቀበሌ ቡጌ ሀ ምርጫ ጣብያ 20 ወንድ እና 9 ሴቶች በአጠቃላይ 29 መራጮች እንዳይመርጡ የተከለከሉባቸው ሁኔታዎች ነበሩ። እነዚህ ሁኔታዎች በመጀመሪያ ደረጃ መራጮቹ ይዘው የተገኙት መታወቂያ የተሰጠበት ቀን ስድስት ወር ያልሞላው በመሆኑ እንዲሁም እነዚህን መታወቂያዎች ይዘው ወደ ጣቢያዎች የሄዱት ከ18 ዓመት በታች የሚመስሉ በመሆናቸው ሳይመርጡ እንዲመለሱ ተደርገዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ጣቢያዎች ይዘው የመጡት መታወቂያ የተሰጠበት ጊዜ ከስድስት ወር በላይ እንደሆነ የሚያሳይ (በ 2013 ዓ.ም እና 2014 ዓ.ም መሰጠታቸውን የሚገልፁ) ቢሆንም የመታወቂያዎቹ ይዘት ሲታይ አዲስ ፎቶግራፍ እና አዲስ የእጅ ጽሁፍ የያዘ በመሆኑ ምክንያት የጣቢያው ኃላፊዎች እንደዚህ አይነት መታወቂያዎች ይዘው የመጡ መራጮችን እንዳይመርጡ ከልክለዋቸዋል።

ኦኮቶ ሴሬ ምርጫ ጣቢያ ቦሮዳ ዎቻ 22 የሚሆኑ ለመምረጥ የመጡ ዜጐች መታወቂያዎቻቸው የተሰጡባቸው ግዜ በግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. በመሆኑ እንዳይመርጡ ተከልክለዋል። ከእነዚህም ውስጥ በአንዳንዶቹ መታወቂያዎች ላይ የሰፈረው የትውልድ ቀን ከድምጽ መስጫው ቀን (ሰኔ 12) ጋር ሲቀናነስ 18 ዓመት ያልሞላቸው ሆኖ በመገኘቱ ድምፅ እንዳይሰጡ ተደርጓል።

## 4. የመራጮች ምዝገባና ድምጽ መስጠት ሂደት መቋረጥን በተመለከተ

ቦሎሶ ሶሬ ወረዳ፣ ወርሙማ ቀበሌ፣ ቤታሎ ሀ 7 ምርጫ ጣብያ ላይ መታወቂያ ካወጡ ስድስት ወር ያልሞላቸው ድምጽ ለመስጠት የመጡ ዜጎች እንዳይመርጡ በመከልከሉ ለተወሰነ ደቂቃ የምርጫ ሂደቱ ተቋርጦ ነበር።

ኪንጎ ኮይሻ ወረዳ፣ ቱልቻ ቀበሌ፣ ሀ 2 ምርጫ ጣብያ ላይ ለዝናብ እና ለፀሀይ መከላከያ ባለመኖሩ ዝናብ በዘነበበት ወቅት መተረማመስ በመፈጠሩ የምርጫ ሂደቱ ለ40 ደቂቃ ያህል ተቋርጦ ነበር።

## 5. በተከለከሉ ቦታዎች ላይ የተቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች

ኦፋ ወረዳ ገሱባ 01 ቀበሌ 07 ምርጫ ጣብያ የምርጫ ሕጉ ከሚፈቅደው በተቃራኒው በሕክምና መስጫ ተቋማት (ጤና ኬላ) ጣብያ ውስጥ ጣቢያው ተቋቁሟል።

## 6. የቁሳቁሶች አለመሟላት

በዳሞት ጋሌ ወረዳ፣ ቡጌ ቀበሌ ቡጌ ሀ ምርጫ ጣቢያ የቅሬታ መቀበያ ቅጽ እንዳልነበር የኅብረቱ ታዛቢ ሪፖርት አድርገዋል።

# ምዕራፍ 9: የድህረ -ድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ የትዝብት ግኝቶች

ኅብረት ለምርጫ ከሰኔ 20 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ባሉት ቀና አጠቃላይ የፖለቲካ ምህዳሩን፣ የህዝብ አስተያየትን እና የሲቪክ ምህዳር ለመቃኘት 6 የረጅም ጊዜ ታዛቢዎችን አሰማርቶ 24 ሪፖርቶችን ሰብስቧል። የሚከተሉት ግኝቶች በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

## ከሕዝበ ውሳኔ በኋላ የተካሄደ አመጽ እና ተቃውሞ

- ሁሉም የ24(100%) ታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ከህዝበ ውሳኔው ሂደት እና ውጤት ጋር በተያያዙ የመንቀሳቀስ ወይም የመሰብሰብ መብቶች፣ ህዝባዊ ተቃውሞዎች እና ህዝባዊ አመፆች ላይ ምንም ገደብ እንዳልነበረው ያመለክታሉ። በተጨማሪም፣ የሚዲያ ባለሙያዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች/የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መታሰር፣ ማስፈራራት፣ ወከባ፣ ግድያ የጥላቻ ንግግር፣ የስድብ ወይም የዛቻ ንግግር አልነበረም።

## በህዝበ ውሳኔው ውጤት ላይ የነበረ የህዝብ አስተያየት

- ሁሉም የ24(100%) ከታዛቢዎች የተላኩ ሪፖርቶች ከድጋሚ ህዝበ ውሳኔው ምርጫ ውጤት ጋር በተያያዘ የሚዲያ ሽፋን ቃና እና ይዘት ገለልተኛ መሆኑን አመልክተዋል።
- 4 (17%) ከታዛቢዎች የተላኩ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት በህዝበ ውሳኔው በድጋሚ በተካሄደው ውጤት ላይ የማህበረሰብ ውይይቶች (ለምሳሌ የአዳራሽ ስብሰባዎች) ነበሩ።
- 1 (4%) ከታዛቢ የተላከ ሪፖርት ከውጤት ጋር በተያያዘየተጋነኑ ሪፖርቶች፣ የተዛቡ እውነታዎች እና የውሸት ወሬዎች በሪፈረንደም ድጋሚ ምርጫ ላይ እንዳሉ አመልክቷል። ይህ ክስተት የተዘገበው የወላይታ ሶሻል ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ አባል እና የማህበራዊ ሚዲያ አክቲቪስት በማህበራዊ ሚዲያ(ፌስቡክ) መካከል የተካሄደውን የሃሳብ ልውውጥ ተከትሎ የወላይታ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ አባል ህዝቡን 'ጎጆ' አማራጭ እንዲመርጥ እየጠራ ባለበት ወቅት አክቲቪስቱ የሪፈረንደም አማራጮች ለህዝቡ ምንም አይነት ትክክለኛ ትርጉም አይኖራቸውም በማለት ሲሚገት ነበር።

## በሲቪክ ምህዳር ላይ የተጣሉ ገደቦች

- ሁሉም የ24 (100%) ታዛቢዎች ዘገባዎች ከህዝበ ውሳኔው ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት ጋዜጠኞች፣ ታዛቢዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ሰራተኞች ወይም ዜጎች እንዳልታሰሩ ያመለክታሉ።
- 20 (83%) ታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ከሕዝበ ውሳኔ በኋላ በተደረገው የድጋሚ ጊዜ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተሳትፎ እና ተሳትፎ ዝቅተኛ ነበር።

# ምዕራፍ 10: መደምደሚያ እና ምክረ ሃሳቦች

## መደምደሚያ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ በወላይታ ዞን ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄደውን የድጋሚ ህዝበ ውሳኔ የምዝገባና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶችን 117 ተቀማጭ እና 28 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን በማሰማራት ታዝቧል። በዚህ የትዝብት ክንውን ወቅትም ኅብረቱ በአጠቃላይ ሂደቱ ላይ የታዩ አበረታች መሻሻሎች በሚል የለያቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። እነዚህ መሻሻሎችም ምርጫ ቦርድ ለዳግም ህዝበ ውሳኔው ያደረገው ቅድመ ዝግጅት፣ ሂደቱ የምርጫ ህጉን በተከተለ መልኩ መከናወኑ እና ሂደቱ በሰላማዊ ሁኔታ እንዲካሄድ አስቻይ ምህዳር መፍጠር ናቸው።

# ቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት

በወላይታ ዞን በድጋሚ በተካሄደው ህዝበ ውሳኔ ወቅት በሁሉም የወላይታ ዞን ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች የመራጮች ትምህርት ተግባራት ሲከናወኑ ተስተውለዋል። በዞኑ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማህበራት ዞኑን በመከፋፈል የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ሙከራ ማድረጋቸውን የ ኅብረት ለምርጫ የትዝብት ግኝት ያሳያል።

በተጨማሪም በዞኑ የመራጮች ትምህርት ለመስጠት የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል። የመራጮች ትምህርት የሕዝበ ውሳኔውንቀን መቼ እንደሆነ ፣ ለሕዝበ ውሳኔው የቀረቡትን አማራጮች፣ ለመራጭነት አስፈላጊ የሆኑ የመታወቂያ ሰነዶች፣ እንዲሁም ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ በተመሳሳይ ቀን መከናወኑን እና የመሳሰሉትን ጠቃሚ ጉዳዮች ያካተተ ነበር። ይሁን እንጂ የመራጮች ትምህርትን በመስጠት ረገድ ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ። እነዚህ ተግዳሮቶች የሚያጠቃልሉት፡ የተገለሉ ቡድኖች ተደራሽነት ውስንነት፣ የቋንቋ እና የባህል እንቅፋቶች እና የገንዘብ ድጋፍ እጥረት በመራጮች ትምህርት ጥራት እና ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል።
በቅድመ-ህዝበ ውሳኔ ጊዜ ቅስቀሳዎች እንደነበሩ ታዛቢዎች ጠቁመዋል። ነገር ግን፣ ቅስቀሳዎቹ የተካሄዱት ውስን የአቅርቦት ዘዴዎችን በመጠቀም ሲሆን በዋናነት የመንገድ ዳር ዘመቻዎችን በመጠቀም እና የታተሙ ቁሳቁሶችን በመለጠፍ ብቻ በመሆኑ ውሱን ተደራሽነት ነበራቸው። ቅስቀሳዎቹ የተካሄዱት በከተማዎች ውስጥ መሆኑን እንዲሁም የሪፈረንደም አማራጮችን በበቂ ሁኔታ አለመሸፈናቸውን ለመረዳት ተችሏል። በተጨማሪም በህዝበ ውሳኔው ላይ የተካሄዱት ቅስቀሳዎች ለህዝቡ ያሉትን አማራጮች እኩል አላቀረቡም። የኅብረት ለምርጫ ትዝብት ግኝት እንደሚያሳየው ቅስቀሳዎቹ በዋናነት አዲስ ክልላዊ መንግስት መመስረትን የሚወክለውን የ የ'ነጭ ዕርግብ' አማራጭን የሚደግፉ ነበሩ።

የኅብረት ለምርጫ የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች ከህዝበ ውሳኔው ጋር በተገናኘ በምርጫ ቦርድም ሆነ በሲቪል ማህበራት የተዘጋጁ ክርክሮች እንዳልነበሩ ገልጸዋል። ሆኖም ግን በአገር ውስጥ ራዲዮ ጣቢያ ተዘጋጅቶ የተላለፈ ክርክር እንደነበር ገልጸዋል። ይሁን እንጂ በክርክሩ የተሳተፉ ተከራካሪዎች አቋማቸውን እንዲያቀርቡ የተሰጣቸው ዕድል እኩል ካለመሆኑ ጋር የተያይዙ ክፍተቶች ፣ የክርክሩ አወያይ ባነሷቸው ጥያቄዎች ውስጥ የተስተዋሉ የአወያዩ ወገንተኝነት፣ የሪፈረንደም አማራጮች ብዙም ትኩረት አልመሰጠት እና ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት የሕዝበ ውሳኔው ክርክር የሚከናወንበትን መመሪያዎች ማስተላለፍ ካለመቻሉ ጋር የተገናኙ መጠነ ሰፊ ክፍተቶች ተስተውለዋል።

በአጠቃላይ በቦሎሶ ሶሬ ወረዳ አንድ ለ‹ጎጆ› የቅስቀሳ ፅሁፎችን የለጠፈ ሰው በፖሊስ ከተያዘበት አንድ ክስተት በስተቀር በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሚዲያዎች እና ሲቪል ማህበረሰብ ላይ ምንም አይነት ገደብ፣ ክልከላ፣ ማስፈራራት እና ጥቃት አልደረሰም። በህዝበ ውሳኔው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ሚና በተመለከተ የኅብረት ለምርጫ የሎምልከታ እንደሚያሳየው የሲቪል ማህበራት በምርጫ ታዛቢነት እና በመራጮች ትምህርት ላይ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። እነዚህ ሚናዎች ግን በከተሞች አካባቢ ያተኮሩ ነበሩ።
በሌላ በኩል በቅድመ ሕዝበ ውሳኔ ወቅት የወረዳና የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች በዜጎች ድምጽ ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር በማለም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተስፋ ቃል በመስጠት፣ ዜጎችን በማስፈራራት የያዙትን የመንግስት ኃላፊነት በሕዝበ ውሳኔው ላይ ጫና ለማሳደር ሲሞክሩ ተስተውሏል። የሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን መከልከል፣ የጤና አጠባበቅ እና የግብርና ግብአት አቅርቦትን በመጠቀም ዜጎች ድምጻቸውን ለ‹እርግብ› አማራጭ እንዲሰጡ ለማድረግ ሲሞክሩ ተስተውሏል። በተጨማሪም የወላይታ ዞንን የአዲሱ ክልል ርዕሰ መዲና ለማድረግ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ፣ የስራ እድል ለመፍጠር እና የበጀት ችግሮችን ለመፍታት ቃል የተገባላቸው ዜጎች 'ርግብን' እንዲመርጡ ሲቀሰቀሱ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

## የሕዝበ ውሳኔ ትዝብት

በጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም ከተከናወነው ሕዝበ ውሳኔ ጋር ሲነፃጸር ኅብረቱ የሚከተሉትን ጠንካራ ጐኖች ለማንሳት ይወዳል

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከፀጥታ ማስከበር እና የምርጫ ቁሳቁስ ስርጭት አንፃር ያደረገው ዝግጅት አመርቂ መሆኑ፣ እንዲሁም አብዛኛዎቹን የምርጫ አስፈፃሚዎች ከወላይታ ዞን ውጪ መመልመሉ አዎንታዊ ሁነት ነው፤
2. ጥር 29 ቀን 2015 ዓም ከተካሄደው የህዝበ ውሳኔ ድምፅ አሰጣጥ አንፃር የምርጫ ቦርድ የዳግም ሕዝበ ውሳኔው የመራጮች ምዝገባ እና ድምፅ መስጠት ሂደትን በአንድ ቀን ማከናወኑ ከህግ አግባብ ውጪ የነበረን የድምፅ አሰጣጥ ሁኔታ በመከላልከል ረገድ የጐላ ሚና ነበረው፤
3. ኅብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ከሞላ ጐደል በሁሉም ጣቢያዎች 5 የምርጫ አስፈፃሚዎች መገኘታቸው፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጥንካሬ እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረት ለምርጫ ቦርዱ ሊመለከታቸው ይገባል ያላቸውን አንዳንድ ክፍተቶችን ተመልክቷል። ኅብረት ለምርጫ በወላይታ ዞን በድጋሚ ከተካሄደው ህዝበ ውሳኔ ትምህርት በመውሰድ የሚከተለውን ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል፡-

የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥን በአንድ ጊዜ ከማካሄድ ጋር የተያያዙ እና ማንነትን የማረጋገጥ ችግሮች ማለትም ከተሰጡ ስድስት (6) ወራት ያልሞላቸው የመታወቂያ ካርዶች እና ያለዕድሜያቸው ድምጽ የሚሰጡ ሰዎች በወላይታ ዞን በተካሄደው ድጋሚ ህዝበ ውሳኔ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ናቸው።

ሕዝበ ውሳኔው ከሚካሄድበት ቀን ቀድሞ በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ የተሰጡ መታወቂያ ካርዶችን መያዝ የኅብረቱ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ትልቅ ተግዳሮት በምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ መደቀኑ ታይቷል። ይህ ክስተት ቁጥሩ እየጨመረ በመምጣቱ የምርጫ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 1163 አንቀጽ 18 (1) (ሐ) አንድ ሰው “ቢያንስ ስድስት (6) ወር በምርጫ ክልሉ ውስጥ ከኖረች” በመራጭነት ለመመዝገብ እንደሚችል/እንደምትችል የሚደነግገውን አንቀጽ መሠረት በማድረግ ሕዝበ ውሳኔው ከተካሄደበት ቀን በፊት በነበሩት ስድስት ወራት ወዲህ የተሰጠ መታወቂያ ካርድ የያዙ መራጮች ድምጽ እንዳይሰጡ የሚከለክል መመሪያ ለምርጫ አሰፈፃሚዎች እንዲያወጣ አስገድዶታል። ይህ ክስተት ኅብረት ለምርጫ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በአንዳንዶቹ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንዲቋረጥ አስገድዷል። ከተሰጡ ስድስት ወራት ያልሞላቸው መታወቂያዎችን የያዙ መራጮች ሳይመርጡ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ አንዳንዶች የአዋጅ ቁጥር 1163/19 አንቀጽ 21(4)ን “በሶስት ሰዎች ምስክርነት” የሚለውን ድንጋጌ መሰረት አድረገው እርስ በእርስ እየተመሰካከሩ ተመዝግበው ድምጽ ሰጥተዋል። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎችም እንዳይመዘገቡ የተከለከሉት አንዳንድ ሰዎች አንዳቸው ለሌላቸው ምስክሮች በመሆን ተመዝግበው ድምጽ መስጠታቸውን አረጋግጠዋል። ኅብረት ለምርጫ የምርጫ ቦርድ ህጉን ለማስከበር እና በዚህም የምርጫ ማጭበርበርን ለመከላከል እያደረገ ያለውን ጥረት እያደነቀ አጥፊዎች በቀላሉ ሊጠቀሙበት የሚችሉበት የህግ ክፍተት አሁንም መኖሩን ለመግለፅ ይወዳል።

## የድህረ -ሕዝበ ውሳኔ ትዝብት

የድህረ ሕዝበ - ውሳኔው ወቅት በጠቅላላው ሰላማዊ የነበረ ሲሆን በመንቀሳቀስ እና በመሰብሰብ መብቶች ላይ ማንኛውንም አይነት ገደብ ሲጣል አልተስተዋለም ነበር።በተጨማሪም በህዝበ ውሳኔ ጋር በተገናኘ በጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ የደረሱ የእስር ተግባራት መኖራቸው የሚያስረዱ ሪፖርቶች አልደረሱንም።

# ምክረ-ሃሳቦች

## 1. መራጮች ትምህርትን በተመለከተ

የቅድመ-ሕዝበ ውሳኔ አጠቃላይ ሁኔታ በምርጫ ሂደቶች እና ውጤቶች ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ እንዳላቸው በማመን ኅብረት ለምርጫ በቅድመ-ምርጫ ጊዜ ውስጥ የመራጮች ትምህርት አቅርቦትን፣ የቅስቀሳ ተግባራት እና የክርክሮች አዘገጃጀት ለማጠናከር ያለመ ምክረ ሃሳቦችን ያቀርባል።

- የመራጮች ትምህርት ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለሌሎች የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽነታቸው ውስን እንደነበሩ የታዛቢዎች ሪፖርቶች አረጋግጠዋል። በተወሰነ ደረጃም የቋንቋ እንቅፋቶች በመኖራቸው ምክንያት መልዕክቶችን ለመራጮች ለማስተላለፍ ውስንነቶች አጋጥመዋል። ምርጫ ቦርድም ሆነ ሲቪል ማኅበራት የቋንቋ ችግርን ተቋቁመው የመራጮች ትምህርት ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለሌሎች የተገለሉ ወገኖች ተደራሽ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው ሲል ይመክራል።
- የመራጮችን ትምህርትን ከማስራጨት አኳያ የጊዜ እጥረት የነበረ ቢሆንም ምርጫ ቦርድ እና የሲቪል ማህበራት የመራጮች ትምህርትን ለማዳረስ ያደረጉት ጥረት አበረታች ነበር። በሌላ በኩል አብዛኞቹ ታዛቢዎች በታዘቧቸውን አካባቢዎች የመራጮች ትምህርት በቅድመ ሕዝበ ውሳኔ ወቅት ለአንድ ጊዜ ብቻ መሰጠቱን አመልክተዋል። በሁሉም መስፈርቶች እና ዓላማዎች ይህ በቂ አይደለም። በተጨማሪም፣ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የታዛቢዎች ሪፖርት የመራጮችን ትምህርት ጥራት ፍትሃዊ ነው በማለት የገመገሙ ሲሆን ይህም ሲሰጡ የነበሩ የመራጮች ትምህርት ፕሮግራሞች በጣም ጥሩ ወይም መጥፎ እንዳልነበሩ ያሳያል። በሌላ አነጋገር የመራጮች ትምህርት አሰጣት መንገዶች እና ጥራት ሊሻሻል የሚገባቸው ነገሮች መረዳት ይቻላል። ምርጫ ቦርድም ሆነ የሲቪል ማኅበራት በቂና ጥራት ያለው የመራጮች ትምህርት ለዜጎች እንዲደርስ በትኩረት ሊሠሩ ይገባል ሲል ኅብረት ለምርጫ ይመክራል።
- ፍትሃዊ የቅስቀሳ ሁኔታ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ምርጫ ቦርድ በህዝበ ውሳኔ ወቅት በሁለቱም አማራጮች ፍትሃዊ የቅስቀሳ ተግባራት መኖራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዘዴዎችን መፍጠር አለበት። የእያንዳንዱ የሕዝበ ውሳኔ አማራጭ ደጋፊ ድጋፍ የሚያደርግለትን አማራጭ የሚወክሉ ቅስቀሳዎችላይ ለመሳተፍ ንቁ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።
- የዜጎችን ግንዛቤ በማሳደግ ረገድ በምርጫ ሂደቶች ውስጥ የሚኖሩ ክርክሮች  የምርጫ ሂደት ወሳኝ ክፍል ናቸው። ከዚህ በመነሳት የመገናኛ ብዙሃን፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ምርጫ ቦርድ እና ሌሎች ፍላጎት ያላቸው አካላት በቀጣይ የምርጫ ሂደቶች ላይ ክርክሮችን ለማዘጋጀት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ አለባቸው። እነዚህ ክርክሮች ሁሉም ፍላጎት ያላቸው አካላት አቋማቸውን እንዲያቀርቡ እና እንዲከራከሩ እኩል እድል መስጠት አለባቸው።.

## 2. የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች በአንድ ቀን መከናወናቸውን በተመለከተ

- ኅብረት ለምርጫ በድጋሚ ሕዝበ ውሳኔ ቀን የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ በተመሳሳይ ቀን መከናወናቸውን ለማወቅ ችሏል። እነዚህ ሂደቶች በምርጫ ሕጉ መሰረት በተለያዩ ጊዜያት መከናወን እንዳለባቸው ተገልጿል። ሁለቱ ሂደቶች ከዚህ በተለየ መልኩ በአንድ ተመሳሳይ ቀን መከናወናቸው የመራጮችሕገ-መንግስታዊ መብቶች ያጣብባል። በመሆኑም ይህ አይነቱ ሂደት በሚቀጥሉ ምርጫዎች እንዳይደገም ኅብረት ለምርጫ ያሳስባል።

## 3. ከቀበሌ መታወቂያ ካርዶች ጋር በተያያዘ

- ምርጫ ቦርድ መታወቂያዎችን ለማጣራት እና ህጋዊ ሰነዶችን ከሀሰተኛ ሰነዶች ለመለየት በቂ ጊዜ እንዲያገኝ በተቻለ መጠን የመራጮች ምዝገባ ከድምጽ መስጫ ቀን ቢለይ፣
- የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ በአንድ ጊዜ በሚካሄድበት ወቅት እንዲሁም በህጉ በተደነገገው የመራጮች ምዝገባ ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ምርጫ ቦርድ ለምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና በሚሰጥበት ጊዜ "በሶስት ግለሰቦች ምስክርነት" መራጮች እንዲመዘገቡ የሚፈቅደውን የአዋጅ ቁጥር 1163/19 አንቀጽ 21(4) እና (5)ን ከመመሪያ 6 አንቀጽ 20(3) ጋር በጣምራ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ለምርጫ አስፈጻሚዎች ቦርዱ በአፅንኦት ማሳሰብ ይኖርበታል፤
- ከህግ በተቃራኒ የቀበሌ መታወቂያ በማውጣት ላይ የተሳተፉ ተዋናዮችን መርምሮ ለህግ ማቅረብ ያስፈልጋል፤

- ለዓመታት ሲካሄድ የቆየውን የብሔራዊ መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ ሂደት እንዲፋጠን ስራ አስፈፃሚውን አካል የማግባባት ስራ ምርጫ ቦርድ እንዲያከናውን

## 4. አካለ መጠን ያልደረሱ ዜጎች ድምጽ መስጠትን በተመለከተ

ምንም እንኳን የምርጫ ህጉ የመምረጥ እድሜ 18 እና ከዚያ በላይ እንዲሆን ቢደነግግም የግለሰቡን አካላዊ ቁመና በመመልከት ብቻ የሰውን ዕድሜ ለመወሰን የተሻለው መንገድ ላይሆን እንደሚችል መገመት ይችላል። የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በትዝብታቸው እንዳመለከቱት የምርጫ አስፈጻሚዎች አንዳንድ መራጮችን አካላዊ ገፅታቸው ላይ በመመርኮዝ ብቻ ድምጽ እንዳይሰጡ ከልክለዋል። የመምረጥን መብት በአካላዊ ገጽታ ላይ በመመርኮዝ ብቻ የመወሰን አሰራር የህግ ድጋፍ ካለመኖሩ በተጨማሪ በመቀንጨር ሳቢያ ዕድሜያቸው ለአካል መጠን የደረሱ ሰዎችን ለመራጭነት በሕግ የተደነገገውን ዕድሜ (18 ዓመት) ያላሟሉ ሊያስመስል ይችላል።
በሌላ በኩል ምርጫ ቦርድም ከዕድሜ በታች የሆኑ መራጮች በህግ ያልተሰጣቸውን መብት እንዳይጠቀሙ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት። እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ወስጥ በማስገባት ኅብረቱ የሚከተሉትን ምክረ ሃሳቦች ያቀርባል ፦

- የምርጫ አስፈፃሚዎችን በአካላዊ ገጽታ ላይ በመመስረት መራጮችን ድምጽ እንዳይሰጡ ከመከልከል የዘፈቀደ ውሳኔን የሚያስቀር አሰራር ቢዘረጋ። ይህንን ዓላማ ለማሳካት የሚረዳው አንዱ መንገድ ለአቅም መጠን ያላደረሱ መራጮች ተብለው የሚጠረጠሩ መራጮችን ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት የልደት የምስክር ወረቀት ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ማደርግ አንዱ ዘዴ ነው።
- ቦርዱ በመራጮች ትምህርት መርሃ ግብሩ በመራጮች እና በፖለቲከኞች ዘንድ ለአካለ መጠን ያላደረሱ ዜጎችን በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲሳተፉ ማበረታታት ስለሚያስከትለውን መዘዝ ግንዛቤ መፍጠር አለበት። በዚህ ድርጊት ውስጥ የሚሳተፉ ወይም ይህንን ድርጊት የሚያበረታቱ ፖለቲከኞችን እና የፖለቲካ ተዋናዮችን አካለ መጠን ያላደረሱ ዜጎች የተሳተፉበት ምርጫ ውጤት ወደ መሰረዝ ሊያመራ እንደሚችል ማስተማር።

## 5. ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጋር በተገናኘ

ኅብረቱ በምርጫ ሕጉ የተቋቋመው የቅሬታ አሰራር ኮሚቴ በጉጉት የተሞላ (Ambitious) እና ለማሳሳካትም አደጋች ነው ብሎ ያምናል። ኅብረቱ ቀደም ሲል ባወጣቸው የምርጫ ትዝበት ሪፖርቶች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን መፍታት እንደሚያስፈልግ አሳስቧል። የመደመጥ መብት የመራጮች ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ስለሆነ እና ዕጩዎች ይህንን መብት ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ይህንን መድረክ መፍጠር ላልተወሰነ ጊዜ ሊራዘም እንደማይችል ለማንም ግልጽ ነው። በወላይታ ዞን በድጋሚ በተካሄደው ህዝበ ውሳኔ ኅብረቱ በታዘባቸው በአብዛኛው የምርጫ ጣቢያዎች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አለመኖራቸውን ታዝቧል። ኅብረቱ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የተቋቋመው 20 በመቶ በሚሆኑት ብቻ መሆኑን ታዝቧል። ከዚህም በላይ፣ የተቋቋሙት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እንዴት እንደተመረጡ እና እንደተሰየሙ፣ ቅሬታዎችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ስልጠና ስለመውሰዳቸው ምንም መረጃ የለም። ከዚህ አኳያ ኅብረት ለምርጫ የሚከተሉትን ምክረ ሃሳቦች ያቀርባል፦

- ቦርዱ በአገሪቱ ባሉ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን በጥናት በመለየት
- ተመሳሳይ የዕድገት ፤ የማንበብ እና መጻፍ ደረጃ ላይ የሚገኙ አገሮችን መነሻ(ቤንች ማርክ ) በማድረግ አሁን በስራ ላይ በሚገኘው የቅሬታ አሰማም ስርአት ላይ የህግ ማሻሻያ ማድረግ።

## 6. የሲቪል ማህበራት ሚና

የሲቪል ማህበራት በወርሃ ጥር 2015 ዓ.ም በስድስት ዞኖች እና አምስት ልዩ ወረዳዎች እንዲሁም በሰኔ ወር 2015 ዓ.ም በወላይታ ዞን በተካሄደው ድጋሚ ሕዝበ-ውሳኔ የነበራቸው ሚና እጅግ አነስተኛ ነበር። በጠቅላላ ምርጫ ላይ ከሚኖራቸው ተሳትፎ ባለፈ ሲቪል ማህበራት በተለያዩ እንደ ምርጫ ትዝብት እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ባሉ የምርጫ ተግባራት መሳተፍ አለባቸው።

# ኅብረት ለምርጫ

## የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

ይህ ሪፖርት ሊሳካ የቻለው በነዚህ አጋር ድርጅቶች እርዳታ ነው፡፡


**የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ)**

ስድስት ኪሎ፣ አንጎላ መንገድ፣ ሊደር ሺፕ ኢንስቲትዩት ሕንጻ፣ 2ኛ ፎቅ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

+251 11 811 1455
www.cecoe.org
info@cecoe.org
twitter/facebook: @cecoeEth